# በልዩ ትምህርት ውስጥ የወላጅ መብቶች መመሪያ



## የልዩ ትምህርት የአሰራር ጥበቃዎች ማስታወቂያ

ሴፕቴምበር 2024





Ohio Department of Education & Workforce

ስለ ልዩ ትምህርት ........ 2

ለልዩ ትምህርት የርስዎ ትምህርት ቤት የማግኛ አድራሻ ........ 2

የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ለልዩ ትምህርት የማግኛ አድራሻ ........ 2

ለዚህ የወላጆች መብት መመሪያ የሚሆን መግቢያ ........ 3

አጠቃላይ መረጃ ........ 4

በመረጃ የተደገፈ የወላጅ ፈቃድ ........ 4

በመረጃ የተደገፈ የወላጅ ፈቃድ ለመስጠት፣ የትምህርት ኤጀንሲው፡- ........ 5

ልጅዎ ልዩ ትምህርት ለማግኘት ብቁ ነውን? ........ 6

ገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች (IEE) ........ 7

የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ........ 8

ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ........ 8

የትምህርት መዝገቦች ........ 10

የመዝገቦች ተደራሽነት ........ 10

ክርክርን መፍታት ........ 12

ክርክርን የመፍታት ሂደት ........ 12

የቅድመ ቅሬታ መፍትሔ ........ 13

ማመቻቸት ........ 13

ሽምግልና ........ 15

የግዛት ቅሬታ ማቅረብ ........ 16

የፍትህ ሂደት ቅሬታ ማቅረብ ........ 19

የፍትህ ሂደት የጊዜ ሰሌዳ እና ሂደት ........ 21

በቂነት ........ 21

የመፍትሔ ጊዜ ........ 22

የፍትህ ችሎት ሂደቱ ........ 23

የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ቅሬታዎች እና የጊዜ ሰሌዳ ........ 24

ውሳኔን ይግባኝ ማለት ........ 24

በፍትህ ሂደት ችሎት ወቅት የልጅ ሁኔታ ........ 25

የአቃቤ ህግ ክፍያዎች ........ 26

ዲሲፕሊን ........ 27

የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ልጆች የሚሆኑ የዲሲፕሊን ሂደቶች ........ 27

የባህርይ መገለጫን የመወሰን ስብሰባ ........ 28

ጊዜያዊ አማራጭ (ጊዜያዊ እና ልዩ ልዩ) የትምህርት ሁኔታ ........ 29

በሕዝብ ወጪ በግል ትምህርት ቤት በወላጆች የአካል ጉዳተኛ ልጆችን በአንድ ወገን መመደብ ........ 31

የገንዘብ ማካካሻን የመወሰን ሂደት ........ 31

የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተማሪዎች ስለ ስኮላርሺፕ ፕሮግራሞች ለወላጆች ማሳወቂያ ........ 32

ማሳወቂያው ሲከሰት ........ 32

# ስለ ልዩ ትምህርት

ልዩ ትምህርት፣ ከ 3 እስከ 21 ዓመት ባለው ዕድሜ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ በፌዴራልና በግዛት መስፈርቶች የሚመራ ነው። የፌዴራሉ መስፈርቶች የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ (IDEA) ተብለው ይጠራሉ። የግዛት መስፈርቶቹ የኦሃዮ ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርት የሥራ ሂደት መስፈርቶች (የኦሃዮ የሥራ ሂደት መስፈርቶች) ተብለው ይጠራሉ።

ይህ መመሪያ በ IDEA እና በኦሃዮ የሥራ ሂደት መስፈርቶች መሰረት የእርስዎን መብቶች እና የልጅዎን መብቶች ለመረዳት ሊረዳዎ ይችላል። በተጨማሪም የልጅዎን የልዩ የትምህርት ድጋፎችና አገልግሎቶችን እንድትረዱ የሚረዳዎትን መረጃና ግብዓት ይሰጣችኋል።

የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (ለምሳሌ፣ የትምህርት ቤትዎ ዲስትሪክት) እርስዎ በዚህ ሕግ ሥር ያሉ መብቶችዎን እንዲረዷቸው ሊረዳዎት ይችላል። በዚህ መመሪያ ውስጥ ያለውን መረጃ በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የትምህርት ኤጀንሲዎ የልዩ ትምህርት ዳይሬክተርን ያነጋግሩ።

## ለልዩ ትምህርት የርስዎ ትምህርት ቤት የማግኛ አድራሻ

*እባክዎ በዚህ መስተጋብራዊ ክፍል የሚከተሉትን መረጃዎች ይጨምሩ፡-*
የትምህርት ኤጀንሲ፡-
የልዩ የትምህርት ዳይሬክተር፡-
ስልክ ቁጥር፡-
የኢሜይል አድራሻ፡-

## የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ለልዩ ትምህርት የማግኛ አድራሻ

(ስልክ) 614-466-2650
(ከክፍያ ነፃ) 877-644-6338
(ፋክስ) 614-728-1097

25 S. Front Street
Mail Stop 409
Columbus, Ohio 43215
ተጨማሪ አገናኝ መረጃ

Exceptionalchildren@education.ohio.gov

በቴሌታይፕራይተር (TTY) ለሚጠቀሙ ሰዎች በኦሃዮ ሪሌይ አገልግሎት (800) 750-0750 ይደውሉ።

# ለዚህ የወላጆች መብት መመሪያ የሚሆን መግቢያ

የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ (IDEA) የአካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎችን መብትና የወላጆቻቸውን መብት ይጠብቃል። ይህ መመሪያ ስለ እነዚያ መብቶች ይነግርዎታል። ልጅዎ የልዩ የትምህርት አገልግሎት የሚቀበል ከሆነ ትምህርት ቤትዎ በየዓመቱ አንድ ጊዜ የመመሪያውን አንድ ቅጂ ሊሰጥዎት ይገባል። እርስዎም ቅጂ መቀበል አለብዎት፡-

- ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ሊሆን ይችላል ብለው ስለሚያስቡ ልጅዎ እንዲገመገም ከጠየቁ
- የትምህርት ኤጀንሲዎ ልጅዎ አካል ጉዳተኛ ሊሆን ይችላል ብሎ ስለሚያስብ ልጅዎ እንዲገመገም ከፈለገ
- እርስዎ በኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) በልዩ ልጆች ቢሮ በኩል - በጽሁፍ - ቅሬታ ካቀረቡ (ካስገቡ)፣ እና ይህም በትምህርት ዓመቱ የመጀመሪያ ቅሬታዎ ከሆነ።
- የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ ለፍትህ ሂደት ችሎት በኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) በልዩ ልጆች ቢሮ በኩል - በጽሁፍ - ጥያቄ ካቀረቡ (ካስገቡ)፣ እና ይህም በትምህርት አመቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠይቁ ከሆነ።
- ልጅዎ በዲሲፕሊን (በባህሪ) ምክንያቶች ከትምህርት ቤት ከታገደ – እና አሁን ባለው የትምህርት ዓመት ልጅዎ ከ 10 ቀን ወይም ከዚያ በላይ ከትምህርት ቤት የታገደ ከሆነ
- በማንኛውም ጊዜ የመመሪያውን ቅጂ ሲጠይቁ



# አጠቃላይ መረጃ

## በመረጃ የተደገፈ የወላጅ ፈቃድ

ማንኛውም ሰው ልጅን ለልዩ ትምህርት ግምገማ ሪፈር ማድረግ ይችላል። እርስዎ፣ ወላጅ የሆኑት፣ ስለ ልጅዎ መማር፣ እድገት፣ ወይም አሰራር ስጋቶች በሚኖሩዎት ጊዜ ሁሉ የልዩ ትምህርት ግምገማ ለልጁ መምህር፣ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ እና ለልዩ የትምህርት ተቆጣጣሪ ወይም አስተዳዳሪ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርብዎታል። አንዴ ትምህርት ቤቱ ጥያቄውን ከተቀበለ፣ ት/ቤቱ ለመገምገም ወይም ላለመገምገም ያለውን ፍላጎት በተመለከተ ለእርስዎ ምላሽ ለመስጠት 30 ቀናት አሉት። አንድ ወላጅ የግምገማውን ሂደት ለመጀመር በጽሑፍ ፈቃድ መስጠት አለበት።

አንድ ልጅ ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ ሆኖ ከተወሰነ በኋላ፣ ከግምገማ ቡድኑ ሪፖርት (ETR) በተገኘ መረጃ መሰረት ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ይዘጋጃል። IEP ልጅዎ በትምህርት አመቱ የሚሰራባቸውን የትምህርት ግቦች እና አላማዎች የሚዘረዝር የመግለጫዎች ሰነድ ነው። እንዲሁም ልጅዎ በIEP ውስጥ የተገለጹትን ግቦች ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ድጋፎች እና አገልግሎቶች ይዘረዝራል።

ልጅዎ የIEP ቡድን ይመደብለታል፣ አባላቱም የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ወላጅ(ጆች)
- ቢያንስ አንድ የአጠቃላይ ትምህርት መምህር (ልጁ መደበኛ የትምህርት አካባቢ ውስጥ እየተሳተፈ ከሆነ ወይም ምናልባት የሚሳተፍ ከሆነ)
- ቢያንስ አንድ የልጁ የልዩ ትምህርት መምህር ወይም አቅራቢ
- ብቃት ያለው የትምህርት ኤጀንሲ ተወካይ
- የግምገማ ውጤቶችን የማስተማር አንድምታዎች መተርጎም የሚችል ግለሰብ
- በወላጅ ወይም በትምህርት ኤጀንሲው ውሳኔ፣ ልጅን በሚመለከት ዕውቀት ወይም ልዩ እውቀት ያላቸው ሌሎች ግለሰቦች ከሆኑ፣ እንደ አስፈላጊነቱ የተዛማጅ አገልግሎቶች ሰራተኞችን ጨምሮ
- አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ የአካል ጉዳተኛ የሆነው ልጅ ከሆነ

**የIEP ግምገማ፡-** የIEP ቡድን IEPን ለመገምገም ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መገናኘት ይጠበቅበታል ነገር ግን IEPን ለመከለስ ብዙ ጊዜ መገናኘት ይችላል፣ በተለይ ልጁ እድገት እያመጣ ካልሆነ። በኦሃዮ ሕግ መሠረት፣ የወላጆች ፈቃድ ልዩ የትምህርት አገልግሎቶችን ለማስጀመር ያስፈልጋል ነገር ግን ከዚያ በኋላ የሚደረጉ የIEP ግምገማዎችን ወይም ክለሳዎችን ተግባራዊ ለማድረግ አያስፈልግም። ይሁን እንጂ፣ ወላጆች በIEP ሂደት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አሁንም አስፈላጊ ነው። በማንኛውም የክለሳ ስብሰባ ላይ ወላጆች አስፈላጊ የIEP ቡድን አባላት ናቸው።

**የወላጅ ተሳትፎ**፡- የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጆች እንደመሆንዎ፣ እርስዎ በእያንዳንዱ የIEP ቡድን ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ማሳወቂያ እንዲደርስዎት እና እድል እንዲሰጥዎት መብት አልዎት። የትምህርት ኤጀንሲው እርስዎ መገኘት እንዲችሉ እና ስብሰባው በጋራ ስምምነት በተደረሰበት ሰዓትና ቦታ ለማስያዝ የስብሰባውን ማሳወቂያ በበቂ ሁኔታ ቀድሞ መስጠት አለበት።

**ምትክ ወላጅ ምንድን ነው?**
ምትክ ወላጅ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ከመሆን እና ከመቀበል ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ የአካል ጉዳተኛ ልጅን ሊወክል የሚችል ግለሰብ ነው።

እርስዎ የሚኖሩበት የትምህርት ኤጀንሲ ከሚከተሉት ውስጥ አንዳቸውም በሚከሰቱበት ጊዜ ምትክ ወላጅ ይሰይማል፡-

- ወላጁን ለይቶ ማወቅ ካልተቻለ
- የትምህርት ድርጅቱ ምክንያታዊ ጥረት ካደረገ በኋላ ወላጁን ማግኘት ካልቻለ
- ልጁ አብሮት የሚሆነው የሌለው ቤት አልባ ወጣት ከሆነ
- ልጁ በመንግስት ጥበቃ ስር ያለ ከሆነ

በመረጃ የተደገፈ የወላጅ ስምምነት ማለት እርስዎ እና/ወይም በትምህርት ኤጀንሲ የተሰየሙት ምትክ ወላጅ እርምጃ እንዲወስድ ለትምህርት ኤጀንሲው በጽሁፍ ፈቃድ ይሰጣሉ ማለት ነው። እንዲሁም በመረጃ የተደገፈ ፈቃድዎ የትምህርት ኤጀንሲ ስለታቀደው እርምጃ መረጃ ሰጥቶዎታል ማለት ነው። የትምህርት ኤጀንሲው በጽሑፍ የሰፈረ በመረጃ የተደገፈ ፈቃድዎን ማግኘት ያለበት፦

- የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልገው መሆኑን ለማወቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ልጅዎን ከመገምገሙ በፊት
- የትምህርት ኤጀንሲው ለልጅዎ በእሱ ወይም በእሷ የመጀመሪያ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም፣ እንዲሁም IEP ተብሎ በሚጠራው፣ ውስጥ የተዘረዘሩትን የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠት ከመጀመሩ በፊት
- የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎ ፍላጎቶች እንደተቀየሩ ለማወቅ ልጅዎን እንደገና ከመገምገሙ በፊት
- የትምህርት ኤጀንሲው ከልጅዎ ጋር ተጨማሪ የግለሰብ ግምገማዎችን ከማካሄዱ በፊት። አንድ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ተግባራዊ የባህሪይ ግምገማ ነው
- የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን የትምህርት ምደባ ከመቀየሩ በፊት። ይህ ማለት በህንፃ መገኛ ቦታ ላይ ለውጥ ማድረግ ማለት አይደለም። ይልቁንም በልጅዎ የትምህርት ፕሮግራም ላይ ያለ ለውጥ ማለት ነው
- የትምህርት ኤጀንሲው ስለልጅዎ መረጃ በግዛት ወይም በፌደራል ህግ ከተዘረዘሩት ውጭ ለሌላ ሰው ከመስጠቱ በፊት

ለዳግም ግምገማ የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋል ምንም እንኳን የIEP ቡድኑ ነባሩ የተማሪው መረጃ በቂ ነው ብሎ ቢወስንም፣ እና ምንም ተጨማሪ ፈተና ባያስፈልግም። ይህም አንዳንድ ጊዜ "የመዝገብ ክለሳ" ዳግም ግምገማ ተብሎ ይጠራል።

**ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ሲከሰት በመረጃ የተደገፈ የወላጅ ፈቃድ አያስፈልግም፦**

- የትምህርት ኤጀንሲው እንደ የግምገማ/የዳግም ግምገማ ሂደቱ አካል በማድረግ ያሉትን የተማሪዎች መረጃዎች እየገመገመ ሲሆን
- የትምህርት ኤጀንሲው ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጡትን ምዘናዎች ከልጅዎ ጋር ሲያካሂድ

# በመረጃ የተደገፈ የወላጅ ፈቃድ ለመስጠት፣ የትምህርት ኤጀንሲው፦

- ውሳኔ ለማድረግ የሚያስፈልገዎትን መረጃ ሁሉ ለእርስዎ ለመስጠት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎን ወይም ሌላ የሚያውቁትን የመገናኛ ዘዴ መጠቀሙን ማረጋገጥ አለበት።
- ለትምህርት ኤጀንሲው አንድን ተግባር እንዲያከናውን በጽሁፍ መረዳትዎን እና መስማማትዎን እና የእርስዎ ፈቃድ ተግባሩን የሚገልጽ መሆኑን፣ እንዲሁም ለሌሎች የሚጋሩትን ማናቸውንም የልጅዎ መዝገቦች እና መዝገቦቹም ለማን እንደሚጋሩ ማረጋገጥ አለበት
- በራስዎ ምርጫ ፈቃድ እየሰጡ መሆኑን፣ እና በማንኛውም ጊዜ ሃሳብዎን መቀየር እንደሚችሉ መረዳትዎን ማረጋገጥ አለበት
- ፈቃድዎን ካነሱ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ፈቃድ በሰጡበት ጊዜ እና ፈቃዱን ባነሱት ጊዜ መካከል የወሰደውን ማንኛውንም እርምጃ መቀልበስ እንደሌለበት መረዳትዎን ማረጋገጥ አለበት

## ፈቃድን ማንሳት

ፈቃድን ማንሳት ማለት ስምምነትዎን ያነሳሉ ማለት ነው። በልጅዎ IEP ውስጥ እንደቀረበው ልጅዎ ከአሁን በኋላ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እንዲያገኝ እንደማይፈልጉ ከወሰኑ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድዎን ማንሳት ይችላሉ። ይህን *በጽሑፍ* ማድረግ አለብዎት።

ከዚያም የትምህርት ኤጀንሲው፦

- ለልጅዎ በIEP ውስጥ ያለውን የልዩ ትምህርት አገልግሎት መስጠት ማቆም አለበት፣ ነገር ግን አገልግሎቱን መስጠቱን ከማቆሙ በፊት፣ የትምህርት ኤጀንሲው አገልግሎቶቹን ሊያቆም መሆኑን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። የትምህርት ኤጀንሲው የሚሰጠው ማስታወቂያ የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይባላል። ይህ የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ በዚህ መመሪያ ገጽ 8 ላይ በሚገኘው የቅድሚያ የጽሑፍ ማስታወቂያ ክፍል የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

አንዴ የትምህርት ኤጀንሲው ለልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎት እንደማይሰጥ ገልጾ ይህን የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከሰጠዎት በኋላ እና አንዴ አገልግሎቶቹ ከቆሙ በኋላ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን ለልዩ ትምህርት ብቁ አድርጎ አይቆጥርም እና በምትኩ ልጅዎን እንደ የአጠቃላይ ትምህርት ተማሪ አድርጎ ይቆጥረዋል።

# ልጅዎ ልዩ ትምህርት ለማግኘት ብቁ ነውን?

በአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ሕግ (IDEA) እና በ Ohio Administrative Codeመሠረት የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ተደርጎ ለመወሰድ፣ ልጅዎ ከታች ከተዘረዘሩት አካል ጉዳቶች ውስጥ አንዱ ሊኖረው ይገባል። ያ የአካል ጉዳት በልጅዎ የትምህርት አፈጻጸም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ይገባል እና ልጅዎ በአካል ጉዳቱ ምክንያት ልዩ ትምህርት እና/ወይም ተዛማጅ አገልግሎቶችን መፈለግ አለበት።

- የአእምሮ ጉዳተኝነት
- የመስማት ችግር
- የንግግር ወይም የቋንቋ እክል
- የማየት ችግር
- የስሜት መረበሽ
- የአጥንት እክል
- ኦቲዝምም
- በአንጎል ላይ የደረሰ ጉዳት
- ሌላ የጤና እክል
- የተለየ የመማር ችግር
- መስማት የተሳነው መሆን
- መስማት የተሳነው-ዓይነ ስውር
- ብዙ የአካል ጉዳቶች
- የእድገት መዘግየት

**የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴ**

እርስዎ የሚታደሟቸው ስብሰባዎች፣ የልጅዎ ግምገማ፣ እና የሚቀበሏቸው ሁሉም ማስታወቂያዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ በሚጠቀሟቸው የመግባቢያ ዘዴዎች መፃፍ ወይም መነገር አለባቸው።

ልጅዎን ለመገምገም የሚያገለግሉ ሁሉም ፈተናዎች እና ሌሎች ቁሳቁሶች በልጅዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን አለባቸው — ወይም ለዲስትሪክቱ ትክክለኛ መረጃ የሚሰጥ ሌላ የመግባቢያ ዘዴ መሆን ይኖርበታል፣ ይህም ልጅዎ በአካዳሚያዊ፣ በእድገት፣ እና በተግባራዊ የሚያውቀው እና የሚሰራው መሆን አለበት፣ ለማቅረብ ወይም ለመስጠት የማይቻል ካልሆነ በስተቀር።

## የትምህርት ኤጀንሲውን ልጅዎን እንዲገመግም ይጠይቁ

በልጅዎ ትምህርት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድር የአካል ጉዳት አለበት ብለው ካሰቡ፣ ልጅዎ ለልዩ ትምህርት ብቁ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን (በ IDEA ስር የአካል ጉዳተኛ ልጅ እንደሆነ ተደርጎ ለመቆጠር) የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን እንዲገመግም መጠየቅ ይችላሉ። የትምህርት ኤጀንሲ ጥያቄዎ በደረሰ በ 30 ቀናት ውስጥ በመረጃ የተደገፈ ፈቃድዎን በማግኘት ወይም የትምህርት ኤጀንሲው የአካል ጉዳተኝነትን የማይጠራጠርበትን ምክንያት የሚያብራራ የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ በማቅረብ ምላሽ መስጠት አለበት። የትምህርት ኤጀንሲው የአካል ጉዳተኝነት መኖሩ ከተጠረጠረ ልጅዎን ለመገምገም በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ ሊጠይቅዎት ይችላል። ያም ሆነ ይህ፣ የትምህርት ኤጀንሲው በመረጃ የተደገፈ ፈቃድዎን በጽሑፍ ካገኘ በኋላ፣ የመነሻ (የመጀመሪያውን) ግምገማውን በ 60 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ አለበት።

### ልጅዎ ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ቢሸጋገር

ልጅዎ በኦሃዮ ውስጥ ከአንድ የትምህርት ኤጀንሲ ወደ ሌላ የትምህርት ኤጀንሲ ከተዛወረ፣ የሚከተለውን ለማድረግ አዲሱ የትምህርት ኤጀንሲ የቀድሞ የትምህርት ኤጀንሲ ግምገማን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ 30 ቀናት ድረስ አለው፦

- ግምገማውን ከቀድሞ የትምህርት ኤጀንሲ ለመቀበል፤ ወይም
- ዳግም ግምገማ ለማድረግ ፈቃድ ለማግኘት

በአዲሱ የትምህርት ኤጀንሲ የሚደረግ ማንኛውም ዳግም ግምገማ የእርስዎ የወላጅ ፈቃድ በተሰጠ በ 60 ቀናት ውስጥ መካሄድ አለበት።

### ልጁ በመንግስት ጥበቃ ስር የሚገኝ ከሆነ

ልጅዎ *በመንግስት ጥበቃ ስር ያለ ከሆነ* እና ከወላጆቹ ጋር የማይኖር ከሆነ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ልጁ አካል ጉዳተኛ ልጅ መሆኑን ለማወቅ የትምህርት ኤጀንሲው የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ለማድረግ የወላጅ ፈቃድ አያስፈልገውም፦

- ይህን ለማድረግ ምክንያታዊ ጥረት ቢደረግም የትምህርት ኤጀንሲው የልጁን ወላጅ ማግኘት ካልቻለ
- የወላጆቹ መብቶች ተቋርጠው ከሆነ፤ ወይም
- የወላጆች መብቶች በዳኛ ለመጀመሪያው ግምገማ ለሚስማማ ግለሰብ ተሰጥተው ከሆነ

## ገለልተኛ የትምህርት ግምገማዎች (IEE)

ገለልተኛ የትምህርት ግምገማ (IEEE) እንዲሁም የውጭ ግምገማ ተብሎም ይጠራል። የትምህርት ኤጀንሲው ለዚህ የውጪ ግምገማ የሚከፍለው በልጅዎ ላይ የራሱን ግምገማ አስቀድሞ አድርጎ ከሆነ እና የትምህርት ኤጀንሲው ባገኘው ነገር እርስዎ ካልተስማሙ ብቻ ነው። ዓላማው ልጅዎ ልዩ ትምህርት ማግኘት ያስፈልገው እንደሆነ ወይም አሁንም ልዩ ትምህርት ማስፈለጉ መቀጠሉን ለማወቅ ነው። ልጅዎን ለዚህ የውጭ ግምገማ የሚገመግመው ሰው ለልጅዎ ትምህርት ኤጀንሲ ሊሰራ አይችልም። እርስዎ፣ እንደ ወላጅ፣ በማንኛውም ጊዜ ለልጅዎ የውጪ ግምገማን የማሰናዳት እና የመክፈል መብት አልዎት። አንዴ የትምህርት ኤጀንሲዎ በልጅዎ ላይ ባካሄደው ግምገማ ካልተስማሙ እና የውጪ ግምገማ እንዲደረግልዎ ከጠየቁ፣ የእርስዎ የትምህርት ኤጀንሲ አላስፈላጊ መዘግየት ሳይኖር ከእነዚህ እርምጃዎች ውስጥ አንዱን መውሰድ አለበት፦

- የትምህርት ኤጀንሲው በራስዎ የልጅዎን የውጪ ግምገማ የት ማግኘት እንደሚችሉ ሊነግሮት እና የትምህርት ኤጀንሲው ለግምገማው እንዲከፍል የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች ማሳወቅ አለበት። አንዴ የትምህርት ኤጀንሲው ከተስማማ እና እርስዎም የውጪውን ግምገማውን ካገኙ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ወጪውን መክፈል አለበት።
- የትምህርት ኤጀንሲው ለፍትህ ሂደት ችሎት ለኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የልዩ ልጆች ቢሮ ጥያቄ ማቅረብ አለበት (ገጽ 20 ን ይመልከቱ) ምክንያቱም ኤጀንሲው ከእርስዎ ለውጭ ግምገማ ጥያቄ ጋር አይስማማም። ይህ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የትምህርት ኤጀንሲው ስለ ልጅዎ ያለው የራሱ ግምገማ ትክክል ነው ብሎ ስለሚያስብ ነው።

### ለውጪ ግምገማዎች መስፈርቶች

የትምህርት ኤጀንሲው በሚያደርጋቸው ግምገማዎች ላይ የሚመለከቱት ተመሳሳይ መስፈርቶች እርስዎ ባዘጋጁዋቸው የውጪ ግምገማዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፣ እና የትምህርት ኤጀንሲው ይከፍላል። እነዚህ መስፈርቶች ልጅዎ ለግምገማ የት እንደሚሄድ እና ልጅዎን የሚመረምረው ሰው ልምድን ያካትታሉ። የትምህርት ኤጀንሲው የትምህርት ኤጀንሲውን መስፈርት የሚያሟላን የውጪ ግምገማ ሙሉ ወጪ መክፈል አለበት።

ለልጅዎ የውጪ ግምገማ ከጠየቁ የትምህርት ኤጀንሲው ለምን በትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎ ግምገማ እንደማይስማሙ ሊጠይቅዎት ይችላል (ማለትም፣ የውጪ ግምገማ እንዲደረግ የፈለጉባቸውን ምክንያቶች)፣ ግን ይህን ማስረዳት የለብዎትም፣ እርስዎ ካልፈለጉ በስተቀር። የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን በሚገመግምበት እና በትምህርት ኤጀንሲው የግምገማ ውጤቶች በማይስማሙበት በእያንዳንዱ ጊዜ፣ እርስዎ መብት ያለዎት በትምህርት ኤጀንሲው ለሚከፈል አንድ የውጪ ግምገማ ብቻ ነው።

አንዴ ልጅዎ የትምህርት ኤጀንሲውን መስፈርት የሚያሟላ የውጪ ግምገማ ካደረገ በኋላ፣ ለግምገማው ማንም ይክፈል ማን፣ የትምህርት ኤጀንሲው የግምገማውን ውጤት ከግምት ውስጥ ማስገባት እና ለልጅዎ ነፃ ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) እንዴት እንደሚሰጥ መወሰን አለበት።

# የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ

## አጠቃላይ ዕይታ

የትምህርት ኤጀንሲ አንዳንድ እርምጃዎችን ከማቅረቡ ወይም ከመከልከሉ በፊት ምክንያታዊ በሆነ የጊዜ መጠን ውስጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ (የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይባላል) ሊሰጥዎት ይገባል። እነዚህ እርምጃዎች የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን መለያ፣ ግምገማ ወይም የትምህርት ምደባ ወይም ለልጅዎ ነፃ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት መስጠት መጀመርን ወይም መለወጥን ያካትታሉ። የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ አስፈላጊ የሆነ የልዩ ትምህርት ቅጽ ነው።

## የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይዘቶች

የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመረጃ ላይ በተመሰረተ መንገድ በልጅዎ የትምህርት አገልግሎቶች ውሳኔዎች ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችልዎትን በቂ ዝርዝር ማቅረብ አለበት። የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- በትምህርት ኤጀንሲው የቀረበው ወይም ውድቅ የተደረገው እርምጃ መግለጫ
- የትምህርት ኤጀንሲው ርምጃውን ለምን እንዳቀረበ ወይም እንደማይፈልግ ማብራሪያ
- ትምህርት ቤቱ ውሳኔውን ለመወሰን የተጠቀመበትን የእያንዳንዱ የግምገማ ሂደት፣ ምዘና፣ መዝገብ ወይም ሪፖርት ገለጻ።
- በIDEA የአሰራር ጥበቃዎች ስር ጥበቃ እንዳለዎት የሚገልጽ መግለጫ፣ እና ማስታወቂያው ለግምገማ የመጀመሪያ ሪፈራል ካልሆነ የአሰራር ጥበቃዎችን መግለጫ የሚያገኙበት መንገድ
- የIDEA መስፈርቶችን በመረዳት ረገድ እገዛ ለማግኘት እርስዎ እንዲያነጋግሩ ምንጮች
- የIEP ቡድን ያጤናቸውን ሌሎች አማራጮች እና እነዚያ አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸውን ምክንያቶች
- ከትምህርት ኤጀንሲው የቀረበ ሀሳብ ወይም እምቢተኝነት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ምክንያቶች መግለጫ

## የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለመረዳት በሚያስችል ቋንቋ

የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ለብዙኃኑ ህዝብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ መሰጠት አለበት እና እንዲሁም ይህን ለማድረግ ተግባራዊ ካልሆነ በስተቀር በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የመግባቢያ ዘዴ መፃፍ አለበት።

የአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም ሌላ የመግባቢያ ዘዴዎ የጽሁፍ ቋንቋ *ካልሆነ*፣ የትምህርት ኤጀንሲው የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያውን በቃላት ወይም በሌላ ለመረዳት በሚያስችል መንገድ በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ወይም በሌላ የመግባቢያ ዘዴ ለመተርጎም እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። የትምህርት ኤጀንሲው የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያው በትክክል መተርጎሙን እና እርስዎም ይዘቱን እንደተረዱት በጽሁፍ ማሳየት መቻሉን ማረጋገጥ አለበት።

# ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP)

ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ልጅዎ በትምህርት አመቱ የሚሰራባቸውን የትምህርት ግቦችን እና አላማዎችን የሚዘረዝር የመግለጫዎች ሰነድ ነው። እንዲሁም ልጅዎ በIEP ውስጥ የተገለጹትን ግቦች ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ድጋፎች እና አገልግሎቶች ይዘረዝራል።

የIEP ቡድን አባላት የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- ወላጅ(ጆች)
- ቢያንስ አንድ የአጠቃላይ ትምህርት መምህር (ልጁ በመደበኛ የትምህርት አካባቢ ውስጥ ከሆነ ወይም ሊሳተፍ የሚችል ከሆነ)
- ቢያንስ አንድ የልጁ የልዩ ትምህርት መምህር ወይም አቅራቢ
- ብቃት ያለው የትምህርት ኤጀንሲ ተወካይ

- የግምገማ ውጤቶችን የማስተማር አንድምታዎች መተርጎም የሚችል ግለሰብ
- በወላጅ ወይም በትምህርት ኤጀንሲው ውሳኔ፣ ልጅን በሚመለከት ዕውቀት ወይም ልዩ እውቀት ያላቸው ሌሎች ግለሰቦች ከሆኑ፣ እንደ አስፈላጊነቱ የተዛማጅ አገልግሎቶች ሰራተኞችን ጨምሮ
- አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ፣ የአካል ጉዳተኛ የሆነው ልጅ ከሆነ

**የIEP ግምገማ**፡- የIEP ቡድኑ IEPውን ለመገምገም ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ መገናኘት ይጠበቅበታል ነገርግን IEPን ለመከለስ ለበለጠ ጊዜ መገናኘት ይችላል፣ በተለይ ልጁ እድገት እያሳየ ካልሆነ። በኦሃዮ ውስጥ፣ IEPን ለመተግበር አመታዊ የIEP ግምገማ እና ክለሳ የወላጅን ፈቃድ አይጠይቅም። የወላጅ ፈቃድ የሚፈለገው ለመጀመሪያው IEP ብቻ ነው። እርስዎ ለIEP ዝግጅት ግብዓት በማቅረብ ረገድ ንቁ ሚና ይጫወታሉ እና በIEP ግምገማዎች ላይ እንዲሳተፉ በጣም ይበረታታሉ።

**የወላጅ ተሳትፎ**፡- የአካል ጉዳተኛ የሆነ ልጅ ወላጆች እንደመሆንዎ መጠን፣ በእያንዳንዱ የIEP ቡድን ስብሰባ ላይ ማሳወቂያ የማግኘት እና የመሳተፍ እድል የማግኘት መብት አለዎት። የትምህርት ኤጀንሲው እርስዎ መገኘት እንዲችሉ እና ስብሰባውን በጋራ ስምምነት በተደረሰበት ሰዓት እና ቦታ ለማስያዝ የስብሰባውን ማሳወቂያ በበቂ ሁኔታ አስቀድሞ መስጠት አለበት።



# የትምህርት መዝገቦች

## የመዝገቦች ተደራሽነት

የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ (FERPA) የልጆችዎን የትምህርት መዛግብት የመመርመር እና የመገምገም የተወሰኑ መብቶችን የሚሰጥዎ የፌዴራል ህግ ነው። በFERPA ስር ያሉ መብቶች ተማሪዎ 18 አመት ሲሞላው ወይም ድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (እንደ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ) መከታተል ሲጀምር ከእርስዎ ወደ ተማሪዎ ይተላለፋሉ፣ የትኛውም ቀድሞ ቢከሰት።

### የትምህርት መዝገቦች ምንድን ናቸው?

ስለ ተማሪ የተወሰነ መረጃ በFERPA የተጠበቀ ስለመሆኑ የሚመረኮዘው ነገሩ የትምህርት መዝገብን ትርጉም በማሟላት ላይ ነው። FERPA የትምህርት መዝገቦችን እንደሚከተለው በማለት ይገልጻቸዋል፡-

1. ከአንድ የተወሰነ ተማሪ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ መዝገቦች፣ አንዳንድ ጊዜ በትምህርት ቤቶች በግል ሊለዩ የሚችሉ መረጃዎች ይባላሉ
2. በትምህርት ኤጀንሲ ወይም ተቋም (ለምሳሌ የትምህርት ቤት ዲስትሪክትዎ) ወይም ለዚያ ኤጀንሲ በሚንቀሳቀስ አካል የተያዙ መዝገቦች

### በግል ተለይተው ሊታወቁ የሚችሉ መረጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የልጅዎ ስም
- የቤተሰብ አባል ስም
- የልጃዎ አድራሻ ወይም የቤተሰብ አድራሻ
- የግል መለያ፣ ለምሳሌ የልጅዎ ማህበራዊ ዋስትና ቁጥር፣ የተማሪ ቁጥር ወይም የባዮሜትሪክ መዝገብ
- እንደ የትውልድ ቀን፣ የትውልድ ቦታ፣ የእናት ከማግባቷ በፊት የነበራት የቤተሰቧ መጠሪያ ስም፣ ዘር ወይም ጎሳ ያሉ ልጅዎን የሚለዩበት ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ መንገዶች
- በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ ምክንያታዊ የሆነን ፣ተዛማጅ ሁኔታዎችን በተመለከተ ግላዊ ዕውቀት የሌለውን አንድን ሰው ተማሪውን በምክንያታዊ እርግጠኝነት እንዲያውቅ የሚያስችለው ከአንድ የተወሰነ ተማሪ ጋር የተገናኘ ወይም የሚያገናኝ ብቻውን ወይም በጥምር ያለ ሌላ መረጃ
- ትምህርት ቤቱ የልጅዎን ማንነት ያውቃል ብሎ በሚያምነው ሰው የተጠየቀ መረጃ
- FERPA የገለጻቸው ሌሎች ምሳሌዎች

### የመዝገቦች ጠብቆ ማቆየት እና ምስጢራዊነት

የትምህርት መዝገቦች በብዙ መንገዶች ሊጠበቁ ይችላሉ። አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- በእጅ የተጻፉ
- ህትመት
- ኮምፒውተር
- ቪድዮ ወይም የድምጽ ቴፕ
- ፊልም፣ ማይክሮፊልም፣ ወይም ማይክሮፊሽ

የተማሪ መዝገቦች ምስጢራዊ ናቸው ማለት *የግል* ናቸው ማለት ነው። የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን መዛግብት ሲሰበስብ፣ ሲያከማች፣ ሲለቅ ወይም ሲያጠፋ ግላዊነትን መጠበቅ አለበት።

### የልጅዎን መዝገብ መገምገም

የትምህርት ኤጀንሲው እርስዎ የልጅዎን የትምህርት መዝገቦች ያለአላስፈላጊ መዘግየት እና ከማንኛውም የIEP ቡድን ስብሰባ ወይም እርስዎ ከተሳተፉበት የፍትህ ሂደት በፊት እንዲገመግሙ መፍቀድ አለበት። የትምህርት ኤጀንሲው እርስዎ መዝገቦቹን እንዲገመግሙ እንዲፈቅድልዎት ከጠየቁበት ቀን ጀምሮ ከ 45 ቀናት በላይ መጠበቅ አይችልም።

ስለ *ልጅዎ* በመዝገብ ላይ የሰፈረውን መረጃ ብቻ የመገምገም መብት አለዎት። ስለ ልጅዎ መዝገብ ማብራሪያ እንዲሰጥዎት ትምህርት ቤቱን የመጠየቅ መብት አለዎት። መዝገቦቹን ለመመርመር እርስዎን ወክሎ የሚሠራ አንድ ሰው (እንደ ጓደኛ ወይም ጠበቃ ያለ) የማግኘት መብት አልዎት።

የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን መዛግብት ቅጂዎች ሊሰጥዎ ይችላል፤ ነገር ግን፣ ይህን አለማድረጉ መዝገቦቹን የመገምገም መብትዎን እንዳይጠቀሙ የሚከለክልዎት ከሆነ የትምህርት ኤጀንሲው ቅጂዎችን ሊሰጥዎ ይገባል። ሁልጊዜ በራስዎ ወጪ የመዝገቦችን ቅጂዎች የመቀበል መብት አልዎት።

## በትምህርት መዝገቦች ላይ የሚደረጉ ለውጦች

በልጅዎ የትምህርት መዝገቦች ውስጥ ያለን የተሳሳተ ወይም አሳሳች መረጃን እንዲቀይር የትምህርት ኤጀንሲውን የመጠየቅ መብት አለዎት። በጥያቄዎ መሰረት የልጅዎ ትምህርት ቤት የትምህርት መዝገቦችን መቀየር የለበትም (ስለጠየቁ ብቻ)፣ ነገር ግን ትምህርት ቤቱ ጥያቄዎን *ግምት ውስጥ ማስገባት* አለበት። ትምህርት ቤቱ በጠየቁት መሰረት የልጅዎን መዝገብ ላለመቀየር ከወሰነ፣ ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር ችሎት የማግኘት መብት እንዳለዎት ትምህርት ቤቱ ሊነግሮት ይገባል።

ከችሎቱ በኋላ፣ ትምህርት ቤቱ አሁንም የትምህርት መዝገቦችን ላለመቀየር ከወሰነ፣ በጉዳዩ ላይ ያለዎትን መግለጫ በልጅዎ መዝገብ ውስጥ የማካተት መብት አለዎት። ይህ መግለጫ የልጅዎ ታሪክ አንድ ክፍል ሆኖ መቀጠል አለበት።

## የትምህርት መዝገቦችን ማጋራት

ብዙውን ጊዜ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን ከእርስዎ ውጭ ለሌላ ሰው የሚገልጹ የትምህርት መዝገቦችን ማጋራት ከፈለገ የእርስዎን ፈቃድ በጽሁፍ ማግኘት *አለበት*። ይሁን እንጂ፣ የእርስዎ ፈቃድ የማያስፈልግባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። አንድ የትምህርት ኤጀንሲ መዝገቦችን ለማጋራት የጽሁፍ ፍቃድ ማግኘት *ስለማይኖርበት*ጊዜ የበለጠ ለማወቅ የ FERPA አጠቃላይ መመሪያ ለወላጆችበዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ ድረ-ገጽ www.ed.govላይ ይመልከቱ።

# ክርክርን መፍታት

## ክርክርን የመፍታት ሂደት

የአካል ጉዳተኛ ልጅዎ ትምህርት የሚያሳስብዎት ከሆነ፣ የመጀመሪያው እርምጃ ከትምህርት ኤጀንሲዎ ጋር መስራት ነው። ለመጀመር፣ የተማሪዎን መምህር ወይም የልዩ ትምህርት ዳይሬክተርን ያግኙ። እርስዎ የሚያስቡትን ነገር ለግለሰቡ ይንገሩት። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ስለእርስዎ አሳሳቢ ጉዳይ ካልተስማማችሁ፣ ሁልጊዜም ችግሩን ለመፍታት አብረው መስራት የሚችሉባቸው መንገዶች አሉ።

እነዚህ ሂደቶች የትምህርት ኤጀንሲዎ ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው መደበኛ ስሞች አሏቸው፣ ነገር ግን ይህ መመሪያ እነዚህ ስሞች ምን ማለት እንደሆኑ እና እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ ልጅዎን እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ለመረዳት ይረዳዎታል። የሚከተለው ክፍል ከትምህርት ኤጀንሲዎ ጋር ለመስራት የሚጠቀሙባቸውን እነዚህን ሂደቶች ወይም ዘዴዎች ይገልጻል።

### አስተዳደራዊ ግምገማ

የአካል ጉዳተኛ ልጅዎን ትምህርት በተመለከተ በትምህርት ኤጀንሲዎ ውሳኔ ካልተስማሙ፣ ለኤጀንሲው አስተዳደር ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። በምላሹ፣ የትምህርት ኤጀንሲዎ የበላይ ተቆጣጣሪ (ወይም ተወካይ) አስተዳደራዊ ግምገማ ያካሂዳል። ይህ ግምገማ አስተዳደራዊ ችሎትን ሊጨምር ይችላል ።

ግምገማው እና አስተዳደራዊ ችሎቱ፣ አንዱ ከተካሄደ፣ ለሁሉም አስፈላጊ ተሳታፊዎች በሚሆን ጊዜ እና ቦታ መሆን አለበት። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በግምገማው ወይም በአስተዳደራዊ ችሎቱ ላይ እንዲገኙ ሌሎችን መጋበዝ ትችላላችሁ። ለምሳሌ ያህል፣ የቤተሰብዎን አባላት ወይም ጓደኛዎን፣ ስለ ልዩ ትምህርት እውቀት ያለውን ሰው ወይም ጠበቃ ሊጋብዙ ይችላሉ። ልጅዎ በካውንቲ የእድገት አካል ጉዳተኞች ቦርድ ወይም በሌላ የህዝብ ትምህርት ኤጀንሲ በሚመራ ፕሮግራም ውስጥ እየተማረ ከሆነ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ለአስተዳደራዊ ግምገማ ከቦርዱ ወይም ከኤጀንሲው ጋር መማከር አለበት።

ሁኔታውን ስትገመግሙ፣ ስለ ልጅዎ ትምህርት ያለን አለመግባባት ለመፍታት ሁሉም ጥረት መደረግ አለበት። የበላይ ተቆጣጣሪው (ወይም ተወካይ) የአለመግባባቱን ሁለቱንም ወገኖች ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል። ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ፣ የበላይ ተቆጣጣሪው ስለውሳኔው ለእርስዎ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። ይህ ስለስጋትዎ ለትምህርት ኤጀንሲው ለመጀመሪያ ጊዜ ካሳወቁ በ 20 ቀናት ውስጥ መከናወን አለበት።

### ሊሞክሯቸው የሚችሉ ተጨማሪ ሂደቶች

ይህን ሂደት ከጨረሱ እና እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ችግሩን እንዴት እንደሚፈቱ አሁንም ካልተስማማችሁ፣ እርስዎ ሊሞክሯቸው የሚችሏቸው ተጨማሪ ሂደቶች አሉ። ወደ ሌሎች ክርክርን የመፍታት ሂደቶች ከመሄድዎ በፊት አስተዳደራዊ ግምገማ እንዲደረግ መጠየቅ ባይጠበቅብዎትም፣ ማድረጉ ግን ይበረታታል። ችግሩን ለመፍታት ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸው ተጨማሪ አማራጮች አሉ። የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (The Ohio Department of Education) የልዩ ልጆች ቢሮ ሊሳተፍ እና ለስጋትዎ መፍትሄ ለማምጣት በእርስዎ የተጨማሪ መሰሪያዎች ጥያቄዎ ረገድ ሊረዳዎት ይችላል። የሚከተሉት አካላትም ሊረዱዎት ይችላሉ፦

- የእርስዎ የአካባቢ ግዛት ድጋፍ ቡድን (ክልል #____) በ (ስልክ #____________). በግዛት የድጋፍ ቡድን ውስጥ ያለው የወላጅ እና የቤተሰብ አማካሪ ከእርስዎ ጋር ይሰራል።
- የአካባቢዎ የወላጅ ኮች፣ የትምህርት ኤጀንሲዎ ካለው።
    - የወላጅ ኮች ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ቤተሰቦች እና የትምህርት ኤጀንሲዎች መረጃ እና ድጋፍ ይሰጣል። የወላጅ ኮች የትምህርት ኤጀንሲ ሰራተኛ እና እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ልጅ ወላጅ ነው።
    - ለበለጠ መረጃ፣ ______________________________________ን ያነጋግሩ።
- የኦሃዮ ጥምረት ለአካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርት (Ohio Coalition for the Education of Children with Disabilities (OCECD)
    - OCECD በኦሃዮ ውስጥ ያሉ የጨቅላ ሕጻናት፣ ድክ ድክ የሚሉ ህጻናት፣ ልጆች፣ እና አካል ጉዳተኛ ወጣቶች ቤተሰቦችን እና ለእነሱ አገልግሎት የሚሰጡ መምህራንን እና ኤጀንሲዎችን የሚያገለግል ግዛት-አቀፍ ለትርፍ

ያልተቋቋመ ድርጅት ነው። የOCECD ፕሮግራሞች ወላጆች በሁሉም የትምህርት ተቋማት ለልጆቻቸው በመረጃ የተደገፈ እና ውጤታማ ተወካዮች እንዲሆኑ ያግዛቸዋል።

ለበለጠ መረጃ፣ በ (740) 382-5452 ላይ OCECD ን ያነጋግሩ ወይም www.ocecd.org ላይ የOCECD ድረ-ገጽን ይጎብኙ።

# የቅድመ ቅሬታ መፍትሔ

የቅድመ ቅሬታ መፍትሔ ከትምህርት ኤጀንሲው ጋር ያለዎትን ልዩነት መደበኛ ባልሆነ መንገድ ለመፍታት ሲሞክሩ እና በተለይ ሌሎች ክርክርን የመፍታት አማራጮችን መጠቀም ከመጀመርዎ በፊት ነው። ከኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ለልዩ ልጆች ቢሮ የሆነ አንድ ሰው እርስዎ ስለልጅዎ ትምህርት ያሉዎትን ጥያቄዎች እና ስጋቶች ለመፍታት እንዲችሉ ለመርዳት ከእርስዎ ጋር ይሰራል።

እርስዎ እንደ የጽሁፍ ቅሬታዎች ወይም የፍትህ ሂደት ችሎቶች ያሉትን ተጨማሪ መደበኛ ሂደቶችን ከመጠየቅዎ በፊት፣ ከመጠየቅዎ በፊት የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የቅድመ ቅሬታ መፍትሔን ያበረታታል። ስለልጅዎ ትምህርት ያሉዎትን ጥያቄዎች እና ስጋቶች ለመፍታት እንዲረዳዎ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education  and Workforce) ለልዩ ልጆች ቢሮ ያለን አንድ ሰው ማነጋገር ይችላሉ። ስለ ቅድመ ቅሬታ መፍትሔ ከአንድ ሰው ጋር ለመነጋገር፣ እባክዎ መምሪያውን በሚከተለው ያነጋግሩ።

- በስልክ፦ (614) 466-2650, ወይም በነፃ (877) 644-6338
- በኢ-ሜይል፦ exceptionalchildren@education.ohio.gov

# ማመቻቸት

ስለ ልጅዎ ልዩ ትምህርት ግምገማ ወይም ዳግም ግምገማ፣ ወይም ስለልጅዎ ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የሚያሳስብዎት ከሆነ ማመቻቸት የሚባል አማራጭ ለእርስዎ ሊጠቅም ይችላል።

ማመቻቸት የልጅዎ ግምገማ ወይም የIEP ቡድን ስብሰባ ላይ አመቻች እንዲገኝ እርስዎ መምሪያውን እንዲያዘጋጅ ሲጠይቁ ነው (እርስዎም የዚህ ቡድን አባል ነዎት)። እንዲሁም የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን ልዩ ትምህርት በሚያካትተው በእነዚህ ስብሰባዎች በአንዱ ላይ አመቻች እንዲገኝ ለመምሪያው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው አመቻቹ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ሁለታችሁም መስማማት አለባችሁ።

## የማመቻቸት ዓላማ

ማመቻቸት የሚካሄደው በቡድን ስብሰባ ውስጥ ነው፣ ለምሳሌ የግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም ቡድን ስብሰባ፣ የግምገማ እቅድ ስብሰባ፣ ወይም የግምገማ ቡድን ስብሰባ ውስጥ። አመቻቹ የቡድኑ አባል ያልሆነ እና ለቡድኑ ውሳኔ የማይሰጥ ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ነው። አመቻች መኖሩ ቡድኑ ውጤታማ እንዲሆን እና በተማሪው ላይ እንዲያተኩር ይረዳል። አመቻቾች በልዩ የትምህርት ሂደቶች በየልዩ ልጆች ቢሮ (Office for Exceptional Children) የሰለጠኑ ባለሙያ አስታራቂዎች ናቸው።

በማንኛውም ጊዜ ማመቻቸት መጠየቅ ይችላሉ። አንዴ ከጠያቃችሁ፣ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ሁለታችሁም ለመሳተፍ መስማማት አለባችሁ። ሁለታችሁም ከተስማማችሁ፣ የልዩ ልጆች ቢሮ (Office for Exceptional Children) አንድ አመቻች ይመድብላችኋል። ከእርስዎ ወይም ከትምህርት ኤጀንሲው ለማመቻቸት የሚወጣ ምንም ወጪ የለም።

**አመቻቹ፡-**

- የሶስተኛ ወገን ገለልተኛ ሆኖ ይቆያል (ለእርስዎ ወይም ለትምህርት ኤጀንሲው አይወግንም ወይም አይሰራም)
- በሙያው የሰለጠነ *አስታራቂ*( አለመግባበቶችን ለመፍታት የሚረዳ ብቃት ያለው ሰው)
- ስለ ልዩ ትምህርት ህጎች እና መስፈርቶች ሰለጥኗል እና ያውቃል
- የልጅዎ IEP ወይም የግምገማ ቡድን አባል አይደለም
- ውሳኔዎችን አይሰጥም፣ ነገር ግን ቡድኑን መፍትሔዎችን እንዲያገኝ ይመራዋል
- በእርስዎ እና በትምህርት ኤጀንሲው መካከል ውይይት ለመክፈት ይረዳል
- ስብሰባው መንገዱን ጠብቆ እንዲሄድ ያደርጋል እና ሁሉም ሰው ሂደቱን እንዲያከብር ያግዛል።
- ቡድኑ በልጅዎ እና በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል



**ስለ ማመቻቸት ማስታወስ ያሉብዎት ቁልፍ ነጥቦች፡-**

- ማመቻቸት በፍቃደኝነት የሚሆን ነው።
  - እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የሂደቱ አካል ለመሆን መስማማት አለባችሁ። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በስብሰባ ላይ አመቻች እንዲኖር ከተስማማችሁ፣ ይህ ማለት እርስዎ በስብሰባው ላይ ከትምህርት ኤጀንሲው ጋር መስማማት አለብዎት ወይም ስብሰባው እንዴት እንደሚሆን መስማማት አለብዎት ማለት አይደለም። ወላጆች ምንጊዜም የራሳቸው አመለካከቶች እንዲኖራቸው ይፈቀድላቸዋል ።
- በማመቻቸት ስብሰባ ወቅት የተደረገ ማንኛውም ስምምነት በአጠቃላይ አስገዳጅ ነው። ይህ ማለት ውሳኔው በጋራ ከተወሰነ በኋላ እርስዎም ሆኑ የትምህርት ኤጀንሲው ስምምነቱን መከተል አለባችሁ።
  - እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ስለልጅዎ ግምገማ ወይም ስለ IEP የምትፈርሙት ማንኛውም ሰነድ በማንኛውም ሌላ IEP ወይም የግምገማ ቡድን ስብሰባ ላይ እነርሱ ከፈረሟቸው ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት አለው።

ስለ ማመቻቸት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ድረ-ገጽን ይጎብኙ በ education.ohio.gov and search ***facilitation*።**

**ማመቻቸትን ለመጠየቅ**

ዲስትሪክቱ በዚህ ሂደት ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆኑን ለማየት የትምህርት ኤጀንሲዎን የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ያነጋግሩ፣ _________ በ____________። አንዴ ሁለቱም ወገኖች በማመቻቸት ላይ ለመሳተፍ ከተስማሙ፣ እባክዎን የኦሃዮ የትምህርት እና የሰው ሃይል መምሪያ የ
ልዩ ልጆች ቢሮን ያነጋግሩ፡-

- በስልክ፡- (877) 644-6338
- በኢሜይል፡- OECMediation Facilitation@education.ohio.gov

# ሽምግልና



ሽምግልና እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎን ወይም የአካል ጉዳት እንዳለበት *የሚጠረጠር* ተማሪዎን ትምህርት በተመለከተ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሶስተኛ ወገን ባለሙያ ወደ ስብሰባ እንዲመጣ ስትስማሙ የሚደረግ ነው። ሶስተኛ ወገን ማለት ይህ ሰው፣ እንዲሁም አስታራቂ ተብሎ የሚጠራው፣ ወገንተኛ ሳይሆን እና ለወላጅ ወይም ለትምህርት ኤጀንሲው የማይሰራ ወይም ወክሎ የማይቆም ማለት ነው። ከልጅዎ ልዩ ትምህርት ጋር በተያያዘ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲዎች ሽምግልና አንድ ምርጫ ነው።

## ሽምግልና ነፃ ነው እና በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል።

ሽምግልና በማንኛውም ጊዜ ሊጠየቅ ይችላል። አንዴ ሽምግልና ከተጠየቀ፣ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በሂደቱ ለመሳተፍ ሁለታችሁም መስማማት አለባችሁ። ሁለታችሁም ለመሳተፍ ከተስማማችሁ፣ የልዩ ልጆች ቢሮ አስታራቂ ይመድብላችኋል። ከልጅዎ ልዩ ትምህርት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር እንዴት መፍታት እንዳለበት አስታራቂው ሊነግርዎ አይችልም። ከዚህ ይልቅ፣ አስታራቂው ልጅዎን በሚያሳትፉ ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩ እና መፍትሔ እንዲያገኙ ሁለቱንም ወገኖች ያግዛል።

መደበኛ ቅሬታ ለማቅረብ ከወሰኑ ወይም የፍትህ ሂደት ችሎት ከጠየቁ (ከገጽ 17-28 ይመልከቱ)፣ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ሽምግልናን እንደ መጀመሪያ ደረጃ እንዲመለከቱት ይጠይቅዎታል። እርስዎ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው ለሽምግልና የምታወጡት ምንም ወጪ የለም።

**ሽምግልን ሽምግልና**

እርስዎ ወይም የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ሽምግልና እንዲካሄድ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ። ቅሬታ ካቀረቡ ወይም የፍትህ ሂደት ችሎት ከጠየቁ መምሪያው እንደ የመጀመሪያ ደረጃ ሽምግልና ያቀርባል። እርስዎ እና ዲስትሪክቱ አስታራቂ ለመጠቀም መስማማት አለባችሁ ።

**አስታራቂ መቀበል እና የስብሰባ መርሃግብር ማስያዝ**

አስታራቂው ገለልተኛ ሶስተኛ ወገን ነው። አስታራቂው በተቻለ ፍጥነት የስብሰባ መርሃግብር ያስይዛል። መምሪያው ለአስታራቂው ይከፍላል።

**የሽምግልና ስብሰባ**

እርስዎ እና የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት እያንዳንዳችሁ ስጋታችሁን ታጋራላችሁ። አስታራቂው አለመግባባቱን ለመፍታት እና የመጨረሻ፣ የጽሁፍ ስምምነት ላይ ለመድረስ ይሞክራል። በአጠቃላይ፣ በሽምግልናው ወቅት የተነገረ ምንም ነገር ከስብሰባው ውጭ ሊጋራ ወይም ወደፊት ለሚፈጸሙ የሕግ ሂደቶች ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፣ የተለየ ሁኔታ ካልተተገበረ በስተቀር።

**ስምምነት ላይ ተደረሰ**

በጽሑፍ የሰፈረው ስምምነት አስገዳጅ ነው፤ እና እርስዎም ሆናችሁ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ትፈርሙታላችሁ። አስገዳጅ ማለት እርስዎ እና ትምህርት ቤቱ ስምምነቱን መከተል አለባችሁ፣ እና ፍርድ ቤት ሊያስፈጽመው ይችላል ማለት ነው።

**ስምምነት አልተደረሰም**

በሽምግልና ላይ ስምምነት ካልተደረሰ እና እርስዎ የግዛት ቅሬታ ካቀረቡ፣ የልዩ ልጆች ቢሮ ቅሬታውን ይፈታል። በሽምግልና ላይ ስምምነት ላይ ካልተደረሰ እና እርስዎ ለፍትህ ሂደት ጥያቄ ካስገቡ፣ ቀጥሎ የፍትህ ሂደት ችሎት ይመጣል።

**አስታራቂው፡-**

- የሶስተኛ ወገን ገለልተኛ ሆኖ ይቆያል (ለእርስዎ ወይም ለትምህርት ኤጀንሲው አይወግንም ወይም አይሰራም)
- ውሳኔ ለማድረግ አይፈቀድለትም፣ በምትኩ፣ አስታራቂው እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን ትምህርት በተመለከተ ያለውን ችግር እንድትፈቱ ያግዘዎታል።
- የጽሑፍ የሽምግልና ስምምነት ላይ ለመወሰን ከእርስዎ እና ከትምህርት ኤጀንሲው ጋር ይሰራል
- የሽምግልና ስብሰባው መንገዱን ጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋል እና ሁሉም ሰው ለሂደቱ አክብሮት እንዲኖረው ይረዳል
- ሁሉም ሰው በተማሪው እና በተማሪው ፍላጎት ላይ እንዲያተኩር ያደርጋል
- በእርስዎ እና በትምህርት ኤጀንሲው መካከል ውይይት ለመክፈት ይረዳል

**ስለ ሽምግልና ማስታወስ ያሉብን ቁልፍ ነጥቦች**

- ሽምግልና በፈቃደኝነት የሚደረግ ነው።
    - እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የሂደቱ አካል ለመሆን መስማማት አለባችሁ። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በሽምግልና ለመሳተፍ ከተስማማችሁ፣ ይህ ማለት በስብሰባው ላይ ከትምህርት ኤጀንሲው ጋር መስማማት አለብዎት ወይም ስብሰባው እንዴት እንደሚሆን መስማማት አለብዎት ማለት አይደለም።
- ሽምግልና ምስጢራዊ ነው።
    - በሽምግልና ስብሰባው ላይ የተነገረው ነገር ሁሉ በአጠቃላይ ሚስጥራዊ (የግል) ነው እና በኋላ ላይ ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፣ ልዩ የሆነ ነገር ካልተተገበረ በስተቀር።
- በሽምግልና ወቅት የተደረገ ማንኛውም የጽሁፍ ስምምነት በአጠቃላይ አስገዳጅ ነው። ይህ ማለት እርስዎም ሆኑ የትምህርት ኤጀንሲው ውሳኔው በጋራ ከተወሰነ በኋላ የጽሁፍ ስምምነቱን መከተል አለባችሁ ማለት ነው።
    - እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ስለልጅዎ ግምገማ ወይም ስለ IEP የምትፈርሙት ማንኛውም ሰነድ በማንኛውም ሌላ IEP ወይም የግምገማ ቡድን ስብሰባ ላይ እነርሱ ከፈረሟቸው ሰነዶች ጋር ተመሳሳይ ክብደት አለው።

**ለሽምግልና ጥያቄ ለማቅረብ**

ዲስትሪክቱ በዚህ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆኑን ለማየት የትምህርት ቤት ዲስትሪክቱን የልዩ ትምህርት ዳይሬክተር ያነጋግሩ ________ በ________። አንዴ ሁለቱም ወገኖች በሽምግልና ለመሳተፍ ከተስማሙ፣ እባክዎን የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የልዩ ልጆች ቢሮን ያነጋግሩ፡-

- በስልክ፡- (877) 644-6338
- በኢሜይል፡- OECMediationFacilitation@education.ohio.gov

# የግዛት ቅሬታ ማቅረብ

ለእርስዎ ያለው ሌላው አማራጭ፣ ስለልጅዎ ልዩ ትምህርት ስጋት ካለዎት፣ በትምህርት ኤጀንሲው ላይ መደበኛ የመንግስት ቅሬታ በጽሁፍ ማቅረብ እና ይህን ቅሬታ ለኦሃዮ የትምህርት መምሪያ እና የሰራተኛ ኃይል (Ohio Department of Education and Workforce) የልዩ ልጆች ቢሮ ማቅረብ ነው።

## የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ ምንም ዓይነት ወጪ አይወጣም

የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ ምንም ዓይነት ወጪ አይወጣም። በአጠቃላይ የግዛት ቅሬታ ሂደት ችግሩን ከችሎት መስማት ሂደት በበለጠ በፍጥነት እንዲፈታ ያደርጋል እናም ከችሎት መስማት ሂደት ያነሰ የጠላትነት ስሜት የሚፈጥር (ወይም ያነሰ ግጭታዊ) ነው። የግዛት ቅሬታ ለማቅረብ፣ የተፈረመ የጽሁፍ ቅሬታዎን (የመጀመሪያውን ቅጂ) ወደ ልዩ ልጆች ቢሮ መላክ አለበት፣ እና እና የቅሬታውን ቅጂ በቀጥታ ለትምህርት ኤጀንሲው መላክ አለበት።

የእርስዎ ቅሬታ የፌዴራል ወይም የግዛት ልዩ ትምህርት መስፈርቶችን ጥሷል መባሉን የሚገልጽ (የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች ትምህርት ሕግ ወይም የኦሃዮ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርት ኦፕሬቲንግ ስታንዳርዶችን ጥሷል መባሉን የሚገልጽ) ሀተታን ማካተት አለበት። ቅሬታው የአንድ የተወሰነ ሕግን ስም ወይም ጥቅስ ማካተት አያስፈልገውም፣ ነገር ግን የልዩ ትምህርት መስፈርትን ይጥሳል ብለው

እርስዎ ያመኑትን የትምህርት ኤጀንሲው የወሰደውን የተለየ እርምጃ ወይም ያልወሰደውን እርምጃ መግለጽ ያስፈልገዋል። እንዲሁም፣ የትምህርት ኤጀንሲዎ የልዩ ትምህርት መስፈርቱን ጥሷል ብለው የሚያስቡትን ለመደገፍ በቅሬታው ውስጥ እውነታዎችን ማካተት አለበት።

## የግዛት ቅሬታ አስተያየት

የልዩ ልጆች ቢሮ ገምግሞ፣ አስፈላጊም ከሆነ፣ በአግባቡ የቀረበውን ቅሬታ ይመረምራል እና የትምህርት ኤጀንሲው ከልጅዎ ትምህርት ጋር የተያያዘ የልዩ ትምህርት መስፈርትን ጥሶ እንደሆነ ይወስናል። እንዲሁም፣ ሶስተኛ ወገን – ማለትም፣ ከእርስዎ ሌላ ሰው፣ ወይም ከትምህርት ኤጀንሲው ሌላ ኤጀንሲ ወይም ድርጅት – የትምህርት ኤጀንሲው ተማሪን የሚመለከት የልዩ ትምህርት መስፈርት ጥሷል ብሎ ካመነ፣ ለመምሪያው አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

የግዛት ቅሬታ የልዩ ትምህርት ጥሰት በተፈጸመ *በአንድ አመት* ውስጥ ለመምሪያው በማንኛውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል። ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከአንድ አመት በላይ የተፈጸሙ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ጥሰቶችን የሚገልጽ ማንኛውም ቅሬታ አይመረመርም/አይፈታም።

## መደበኛ የግዛት ቅሬታ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል

የልዩ ትምህርትን በተመለከተ መደበኛ የግዛት ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ፡-

- የግዛት ቅሬታ ቅጽን በ [DEW ክርክርን መፍታት ድረ-ገጽ፤ ላይ ይሙሉ]ወይም
- የቅሬታ ደብዳቤ ይጻፉ እና ወደ መምሪያው በፖስታ ወይም በኢሜል ይላኩ፤ ወይም
- ወደ መምሪያው የልዩ ልጆች ቢሮ በ 1-877-644-6338 ይደውሉ እና የቅሬታ ቅጽ ይጠይቁ፣ እሱን ሞልተው ወደ መምሪያው ይመልሱት።

## ቅሬታዎን የት መላክ እንዳለብዎት

ቅሬታዎ *ለሁለቱም*የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Department of Education and Workforce) የልዩ ልጆች ቢሮ እና ለትምህርት ኤጀንሲ የበላይ ተቆጣጣሪ በአንድ ጊዜ መላክ አለበት።

**በግዛት ቅሬታ ውስጥ ማካተት ያሉብዎት ነገሮች የማረጋገጫ ዝርዝር**

- የትምህርት ኤጀንሲው የፌዴራል ወይም የግዛት ልዩ ትምህርት መስፈርቶችን ጥሷል የሚል መግለጫ
- ቅሬታዎን መሰረት ያደረጉባቸውን ምክንያቶች ጨምሮ የችግሩ መግለጫ
- የእርስዎ አገናኝ መረጃ እና ዋና ፊርማ
- እርስዎ ከአንድ የተወሰነ ተማሪ ጋር በተያያዘ የልዩ ትምህርት ጥሰት አለ ብለው እየከሰሱ ከሆነ
- የተማሪው መኖሪያ ቤት ስምና አድራሻ
- ተማሪው እየተማረ ያለበት ትምህርት ቤት ስም
- በቤት አልባ ልጅ ወይም ወጣት ጉዳይ (በ McKinney-Vento Homeless Assistance ሕግ እንደተገለጸው) የተገኘ የተማሪው አገናኝ መረጃ እና ተማሪው የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም
- ከችግሩ ጋር የተያያዙ እውነታዎችን ጨምሮ ስለ ችግሩ ምንነት የተሰጠ መግለጫ
- ቅሬታው በሚቀርብበት ጊዜ ሶስተኛው ወገን በሚያውቀው እና
- በቀረበለት መጠን ችግሩን ለመፍታት የቀረበ ሀሳብ
- ቅሬታው ፊርማ ሊኖረው ይገባል።

*የማን መሆናቸው ያልተጠቀሰ ቅሬታዎች ተቀባይነት እንደማይያገኙ ልብ ይበሉ።*

የመጀመሪያውን ቅሬታ ለሚከተለው ይላኩት፡-
የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የልዩ ልጆች ቢሮ
Attn: Assistant Administrator of Dispute Resolution Section (ክርክር የመፍታት ክፍል ረዳት አስተዳዳሪ)
25 South Front Street, Mail Stop 409
Columbus, Ohio 43215-4183
በኢሜይል፡- oeccomplaints@education.ohio.gov

### የይቆይ ጊዜ
የይቆይ ጊዜ ማለት በግዛት ቅሬታ ዉስጥ ያሉ ጉዳዮችን ማቆየት ማለት ነው። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በፍትህ ሂደት ችሎት ላይ ከተሳተፉ፣ እና እርስዎ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የግዛት ቅሬታ ካቀረቡ፣ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የግዛቱን ቅሬታ ተይዞ እንዲቆይ ያደርገዋል። በሌላ አነጋገር፣ የግዛት ቅሬታዎን ከመፍታቱ በፊት መምሪያው የፍትህ ሂደቱ እስኪያልቅ ድረስ ይጠብቃል። የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄዎን ካነሱት፣ መምሪያው የግዛቱን ቅሬታ ከየይቆይ ጊዜው አውጥቶ የቅሬታ መፍትሔውን ይቀጥላል።

የፍትህ ሂደት ችሎት ከተከናወነ እና በገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹም (IHO) ውሳኔ ከተሰጠ፣ በሰሚ ሹሙ ውሳኔ ያላገኙ ጉዳዮች አሁንም በእርስዎ ቅሬታ ውስጥ የሚቀሩ ከሆነ ብቻ መምሪያው የግዛቱን ቅሬታ ለመፍታት ከየይቆይ ጊዜው ያስወጣዋል።

## የግዛት ቅሬታ ሂደት
መምሪያው የእርስዎ የግዛት ቅሬታ ሲደርሰው፣ በትክክል እስከቀረበ ድረስ፣ መገምገም ይጀምራል እና እንደ አስፈላጊነቱ፣ አሉ ተብለው የሚታሰቡ የልዩ ትምህርት መስፈርቶች ጥሰት(ቶችን) ይመረምራል። የልዩ ልጆች ቢሮ (The Office for Exceptional Children) ቅሬታዎን ከተቀበለበት ቀን አንሥቶ በ 60 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ መፍታት አለበት።

እንደ የቅሬታ ሂደቱ አንድ አካል፣ የልዩ ልጆች ቢሮ የሚከተሉትን ያደርጋል፡-

- ቅሬታዎን ይገምግም እና በቅሬታዎ ውስጥ ያሉትን ክሶች የመፍታት ስልጣን እንዳለው ይወስናል
- የሚፈታቸው የተባሉትን ክሶች፣ ምርመራን (አስፈላጊ ከሆነ) ጨምሮ ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው በጽሑፍ ይነግራል
- ቅሬታውን ለመፍታት እንደ አማራጭ መንገድ ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው ሽምግልናን ወይም ማመቻቸትን ለመስጠት ያቀርባል
- በቅሬታዎ ውስጥ ስላሉት ክሶች ከእርስዎ እና ከትምህርት ኤጀንሲው ሊፈልገው የሚችለውን ተጨማሪ መረጃ ይጠይቃል
- በእርስዎ እና በትምህርት ኤጀንሲው የተሰጡ ተጨማሪ ሰነዶችን እና መረጃዎችን ይገመግማል፣ የስልክ ቃለመጠይቆችን ያካሂዳል፣ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የልጅዎን የትምህርት ኤጀንሲ ይጎበኛል
- ለቅሬታዎ ምላሽ እንዲሰጥ እና መፍትሔ እንዲያቀርብ ለትምህርት ኤጀንሲዎ እድል ይስጣል
- የልዩ ትምህርት ጥሰት ተፈጽሞ ከሆነ (አስፈላጊ ከሆነ ግምገማውን እና ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ እና ቅሬታዎን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ ከ 60 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ) ስለ ውሳኔው ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው ውሳኔውን የሚያሳውቅ ደብዳቤ ይጽፋል።

### የጊዜ ሰሌዳ ማራዘሚያዎች
መምሪያው የጊዜ ማራዘሚያ ካለ ቅሬታውን ለመፍታት እና ከውሳኔው ጋር ደብዳቤ ለመስጠት ከ 60 ቀናት በላይ ሊኖረው ይችላል። የግዛት ቅሬታውን ለመፍታት የ 60 ቀን የጊዜ ሰሌዳ ማራዘሚያ ሊደረግ የሚችለው፡-

- እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ሁለታችሁም ችግሩን በሽምግልና፣ በማመቻቸት ወይም በሌላ አማራጭ የግጭት አፈታት ዘዴ ለመፍታት መሞከር እንድትችሉ ተጨማሪ ጊዜ እንዲኖራችሁ ስትስማሙ፣ ወይም
- ለየት ያሉ ሁኔታዎች ሲኖሩ (እነዚህም በልዩ ልጆች ቢሮ እንደየጉዳዩ ይወሰናሉ)።

### ተገቢ ያልሆነ የቅሬታ አቀራረብ
የልዩ ልጆች ቢሮ እርስዎ እንዲፈቱ ስለሚፈልጓቸው ጉዳዮች ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎችን ስላላካተቱ የግዛት ቅሬታ በትክክል እንዳላቀረቡ ከወሰነ፣ ወይም የልዩ ልጆች ቢሮ ቅሬታውን የመመርመር ስልጣን ከሌለው፣ የልዩ ልጆች ቢሮው ቅሬታዎን ለመፍታት ለምን እንደማይገፋበት፣ ለዚህ ውሳኔ ምክንያቱን፣ እና፣ አስፈላጊ ከሆነም በትክክል እንደቀረበ እንዲታይልዎት በአዲስ ቅሬታ ውስጥ ማካተት ያለብዎትን መረጃን የሚገልጽ ደብዳቤ ይልክልዎታል።

### ቅሬታውን እንደገና ማስገባት
ቅሬታውን በአዲስ መረጃ እንደገና እያስገቡ ከሆነ፣ የተባለው የልዩ ትምህርት ጥሰት በተፈጸመበት በአንድ አመት ውስጥ ቅሬታውን ለኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) እና የትምህርት ኤጀንሲ መላክዎን ያረጋግጡ። በቅሬታዎ ውስጥ መምሪያው መፍትሔ የመስጠት ስልጣን የሌላቸውን ጉዳዮች ካካተቱ፣ መምሪያው እንደአግባቡ እነዚህን ጉዳዮች ለመፍታት ወደ ግብአቶች ይመራዎታል።

ቅሬታ ማቅረብ

- የተባለው ጥሰት በተፈጸመ በአንድ አመት ውስጥ የቀረበ ቅሬታ።
- ወላጅ ኦሪጅናሉን ለኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) እና ቅጂውን ለትምህርት ኤጀንሲው ይሰጣል።
- ቅሬታ አቅራቢ የልዩ ትምህርት መስፈርት ጥሰቶችን ደጋፊ እውነታዎችን በማቅረብ ይከሳል።

የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ቅሬታውን ይገመግማል

መምሪያው ቅሬታውን ላቀረበው ግለሰብ እና ለትምህርት ኤጀንሲው የእውቅና ደብዳቤ ይልካል።

መምሪያው ቅሬታው በትክክል ካልቀረበ ወይም መምሪያው የመፍታት ስልጣን ከሌለው በቂ ያለመሆን ደብዳቤን ይልካል።

ግምገማ

መምሪያው ሁሉንም ሰነዶች ይገመግማል እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሰነዶችን/መረጃዎችን ይጠይቃል።

መምሪያው እንደ አስፈላጊነቱ አግባብ ያላቸውን ግለሰቦችን ቃለ መጠይቅ ያደርጋል።

መምሪያው የግኝቶችን ደብዳቤ ይልካል

መምሪያው ለእያንዳንዱ ክስ እና የልዩ ትምህርት ጥሰት ስለመኖሩ አለመኖሩ ውሳኔዎችን ይሰጣል።

መምሪያው የትምህርት ኤጀንሲው ጥሶ በተገኘባቸውን ጉዳዮች የማስተካከያ እርምጃዎችን ይሰጣል።

# የፍትህ ሂደት ቅሬታ ማቅረብ

ስለ ልጅዎ ልዩ ትምህርት አንዳንድ ስጋቶችን ከትምህርት ኤጀንሲው ጋር ለመፍታት የሚችሉበት አንዱ መንገድ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄን በቀጥታ ለትምህርት ኤጀንሲው ማቅረብ ሲሆን፣ ይህም ሲደረግ ቅጂውን ወደ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) በማስተላለፍም ነው። ይህን ሲያደርጉ፣ የፍትህ ሂደት ቅሬታ አስገብተዋል (የፍትህ ሂደት ጥያቄ ተብሎም ይጠራል) ማለት ነው።



የፍትህ ሂደት ቅሬታ ማቅረብ የሚችሉ ሌሎች አሉ፡-

- ተማሪ፣ ቢያንስ 18 ዓመት ከሞላው
- የትምህርት ኤጀንሲ

## ጥያቄ ለማስገባት ምክንያቶች

በሚከተሉት የልጅዎ የልዩ ትምህርት ዘርፎች ላይ ለሚነሱ ስጋቶች የፍትህ ሂደት ቅሬታ ሊቀርብ ይችላል፡-

- የአካል ጉዳተኛ የሆነ ልጅን መለየት
- የአካል ጉዳተኛ የሆነን ልጅ ግምገማ
- የአካል ጉዳት ያለበትን ልጅ ለትምህርት ምደባ
- ለልጅዎ ነፃ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) ማድረስ

የፍትህ ሂደቱ ቅሬታ የፌደራል ወይም የግዛት የልዩ ትምህርት መስፈርቶች ተጥሰዋል እና ወላጅ (ወይም የህዝብ ትምህርት ኤጀንሲ ቅሬታውን ያቀረበው) ተከሰቷል ስለተባለው የልዩ ትምህርት ጥሰት ካወቀበት ወይም ማወቅ ካለበት ቀን ጀምሮ ባሉት *ሁለት ዓመታት* ውስጥ መቅረብ አለበት። የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የፍትህ ሂደት ቅሬታ በደረሰው ጊዜ፣ የሚመለከታቸው ወላጆች እና የትምህርት ኤጀንሲ በፍትህ ሂደት ችሎት ላይ የመሳተፍ እድል ሊኖራቸው ይገባል። የፍትህ ሂደት ችሎት የፍትህ ሂደት ቅሬታን ለመፍታት ገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹም በመምሪያው የተመደበበት መደበኛ ሂደት ነው።

## የሚካተተው መረጃ

መምሪያው ተገቢው የፍትህ ሂደት ለመጠይቅ የሚያገለግል ቅጽ ያቀርባል። ጥያቄውን የሚያቀርበው ሰው ወይም የህዝብ ትምህርት ኤጀንሲ የመምሪያውን ቅጽ፣ መጠቀም አይጠበቅበትም ነገር ግን ያ ሰው ወይም ድርጅት የፍትህ ሂደት ቅሬታ ሲያቀርብ ይህን አስፈላጊ መረጃ ማካተት አለበት፡-

1. የተማሪው ስም
2. የተማሪው አድራሻ ወይም የማግኛ መረጃ
3. የትምህርት ኤጀንሲው ስም
4. ልጅዎ ቤት አልባ ከሆነ፣ ለልጅዎ ያለው የማግኛ መረጃ እና ልጅዎ የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም
5. ልጅዎን የሚመለከት ልዩ ችግር መግለጫ እና የችግሩ እውነታዎች
6. ችግሩን ለመፍታት የሚረዱ ሐሳቦች ወይም አስተያየቶች

የፍትህ ሂደት ቅሬታ ከግዛት ቅሬታ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዝርዝር መረጃ መያዝ አለበት (ገጽ 16 ን ይመልከቱ)፤ ነገር ግን ዋናው ፎርማ አያስፈልግም። ለትምህርት ኤጀንሲው እና ለመምሪያው በአካል፣ በፖስታ፣ በፋክስ፣ ወይም በኢሜል ሊደርስ ይችላል። በመጀመሪያው የፍትህ ሂደት ቅሬታዎ ውስጥ ያልተካተቱ ጉዳዮች በፍትህ ሂደት ችሎት ወቅት በሰሚ ሹሙ አይገመገሙም።

### የፍትህ ሂደት ቅሬታን ማሻሻል

የፍትህ ሂደት ቅሬታን ማሻሻል ማለት ቅሬታው አስቀድሞ ለኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ከቀረበ በኋላ ቅሬታውን ማዘመን ነው። የፍትህ ሂደት ቅሬታዎን ማሻሻል የሚችሉት የሚከተሉት ሲሆኑ ብቻ ነው፡-

- ሌላኛው ወገን በተሻሻለው የፍትህ ሂደት ቅሬታ በጽሁፍ ሲስማማ እና በመፍትሔ ስብሰባ ላይ ቅሬታውን ለመፍታት እድል ሲሰጠው (የመፍትሄ ስብሰባ በገጽ 23 ላይ ተገልጿል)፣ ወይም
- የገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ ፈቃድ ሲሰጥ። የፍትህ ሂደት ችሎት ከመጀመሩ ከአምስት ቀናት በፊት የሰሚ ሹሙ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን ከዚያ በኋላ አይሆንም።

# የፍትህ ሂደት የጊዜ ሰሌዳ እና ሂደት

በልጅዎ የትምህርት ኤጀንሲ ላይ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ካቀረቡ፣ የፍትህ ሂደት ቅሬታዎ በደረሰዎት በ 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ እንደዚህ አይነት ማስታወቂያ ቀድሞውኑ ካልሰጠ በስተቀር፣ የትምህርት ኤጀንሲው ስለተከሰሰው የልዩ ትምህርት ጥሰት የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ ወይም ምላሽ ሊሰጥዎ ይገባል።

የትምህርት ኤጀንሲው የሚሰጥዎት የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- ጥያቄዎ ወይም የፍትህ ሂደት ቅሬታዎ ስለምን እርምጃ እንደሆነ መግለጫ። ይህ የትምህርት ኤጀንሲው ሊወስደው የፈለገው እርምጃ ወይም ለመውሰድ ፈቃደኛ ያልሆነው እርምጃ ሊሆን ይችላል። የትምህርት ኤጀንሲው ለምን ርምጃውን መውሰድ እንደፈለገ ወይም እርምጃውን ለመውሰድ ፈቃደኛ እንዳልሆነ በሰጠው ምላሽ ማስረዳት አለበት።
- ልጅዎን ለመገምገም ኤጀንሲው የተጠቀመባቸው የሁሉም ዘዴዎች መግለጫ፣ ስለልጅዎ መዝገቦች፣ እና የትምህርት ኤጀንሲው እርምጃውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ ውሳኔውን ለመወሰን የተጠቀመበትን ሪፖርት ያሳያል።
- የIEP ቡድኑ ለልጅዎ ግምት ውስጥ ያስገባቸው የሌሎች ምርጫዎች መግለጫ እና እነዚያን ምርጫዎች ያልተቀበለበትን ምክንያት(ቶች)
- የትምህርት ኤጀንሲው እርምጃውን ለመውሰድ ወይም ላለመውሰድ ከወሰነው ውሳኔ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የሌሎች ምክንያቶች መግለጫ

የትምህርት ኤጀንሲው ስለ በነፃ ወይም በዝቅተኛ ወጭ ስለሚገኝ የህግ እርዳታ እና ሌሎች ሊያገኟቸው ስለሚችሉ አገልግሎቶችም መረጃ መስጠት አለበት።

እንደ ወላጅ በእርስዎ ላይ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ከቀረበ፣ በ 10 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለቅሬታው ምላሽ መስጠት አለበት። የእርስዎ ምላሽ በተለይ በፍትህ ሂደት ቅሬታ ላይ የተነሱትን ጉዳዮች መፍታት አለበት።

## በቂነት

ሌላኛው ወገን ለሁለቱም ለገለልተኛ ሰሚ ሹሙ እና ቅሬታውን ላቀረበው ወገን ቅሬታው ቅሬታ የማቅረብ መስፈርቶችን አላሟላም (ማለትም በቂ አይደለም) በማለት ካላሳወቀ *በስተቀር*፣ የፍትህ ሂደት ቅሬታው በቂ ነው ተብሎ ይታሰባል (ማለትም፣ በአግባቡ የቀረበ ነው ማለት ነው)። ሌላኛው ወገን የፍትህ ሂደት ቅሬታው በደረሰበት በ 15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የፍትህ ሂደት ቅሬታውን በቂ መሆን በጽሁፍ መቃወም አለበት።

ለምሳሌ፣ ለትምህርት ኤጀንሲዎ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ካቀረቡ (እና ቅጂውን ለኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ካስተላለፉ)፣ የትምህርት ኤጀንሲው ለችሎቱ ሰሚ ሹሙ፣ በጽሁፍ እና በ 15 ቀናት ውስጥ፣ ጥያቄዎ በትክክል የገባ ነው ብሎ እንደማያስብ ገልጾ ካላሳወቀው በስተቀር፣ ቅሬታዎ በቂ እንደሆነ ይቆጠራል። ከዚያም፣ የፍትህ ሂደት ቅሬታዎ በቂ ስለመሆኑ (በገጽ 22 ላይ የተገለጸውን  የፍትህ ሂደት ቅሬታ መስፈርቶች የሚያሟላ መሆኑን)ለመወሰን ችሎት ሰሚ ሹሙ ከትምህርት ኤጀንሲዎ የጽሁፍ ማስታወቂያ ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ አምስት የቀን መቁጠሪያ ቀናት አሉት። ችሎት ሰሚ ሹም የሱን ወይም የሷን ውሳኔ ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው በጽሁፍ በ 15 ቀናት ውስጥ መላክ አለበት/አለባት።

ችሎት ሰሚ ሹሙ የፍትህ ሂደት ቅሬታዎ በቂ እንዳልሆነ ከወሰነ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ፈቃደኛ እስከሆነ እና ሁኔታውን በመፍትሔ መስጫ ስብሰባ ለመፍታት እድል እስካለው ድረስ ወይም ሰሚ ሹሙ ችሎቱ ከመጀመሩ ከአምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ፍቃድ እስከሰጠ ድረስ አዲስ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ለማቅረብ ወይም ዋናውን የፍትህ ሂደት ቅሬታ ለማስተካከል አማራጭ አለዎት።

የፍትህ ሂደት ቅሬታዎን በትክክል ካሻሻሉ፣ የተሻሻለውን ቅሬታ ሲያስገቡ የ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜው ይጀምራል።

## የመፍትሔ ጊዜ

የመፍትሔ ጊዜው  የፍትህ ሂደት ቅሬታ በማቅረቡ እና በትክክለኛው የፍትህ ሂደት ችሎት መካከል ያለው ጊዜ ነው። የመፍትሔ ጊዜው ችሎቱ በይፋ ከመጀመሩ በፊት የልዩ ትምህርት ክርክርን ለመፍታት ለአንድ ተጨማሪ ጊዜ እድል የሚሰጥ የመፍትሔ ስብሰባን ያካትታል። የፍትህ ሂደት ቅሬታ ካቀረቡ ነገር ግን በመፍትሔው ሂደት ውስጥ መሳተፍ ካልቻሉ፣ ይህ የፍትህ ሂደት የጊዜ ሰሌዳዎችን መጀመር ያዘገያል (በጊዜ ሰሌዳዎቹ ላይ ተጨማሪ ከዚህ በታች አለ)።

የመፍትሔው ጊዜ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ (ወይም ቅሬታው በትክክል ከተሻሻለበት ቀን ጀምሮ) 30 ቀናት ነው። የትምህርት ኤጀንሲው 30 ቀናት ባለፉበት ጊዜ የፍትህ ሂደት ቅሬታውን እርስዎን በሚያረካ መልኩ ካልፈታው፣ የፍትህ ሂደቱ ሊቀጥል ይችላል። አንዴ የ 30-ቀን የመፍትሄ ጊዜ ካለቀ በኋላ፣ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ከ 30 ቀናት በላይ ለሚሄድ ሽምግልና ካልተስማማችሁ በስተቀር ለፍትህ ሂደት ችሎቱ እና ለገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ (ገፅ 22 ን ይመልከቱ) ውሳኔ ለመስጠት የ 45 ቀናት የጊዜ ገደብ አለ። እንዲሁም በእነዚያ 30 ቀናት ውስጥ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ምንም አይነት ስምምነት ሊኖር እንደማይችል በጽሁፍ ከተስማማችሁ የ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜው ቀደም ብሎ ሊያበቃ እንደሚችል ልብ ይበሉ።

የትምህርት ኤጀንሲው በ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜ ውስጥ እና የፍትህ ሂደት ቅሬታ በደረሰው በመጀመሪያዎቹ 15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ስብሰባ ማቀድ ይኖርበታል። የትምህርት ኤጀንሲው የመፍትሔ ስብሰባውን በ 15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ካላካሄደ ወይም የመፍትሔ ስብሰባው ላይ ካልተሳተፈ፣ እርስዎ የችሎት ሹሙን የ 45-ቀን የፍትህ ሂደት የጊዜ ሰሌዳውን እንዲጀምር መጠየቅ ይችላሉ። የትምህርት ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት ቅሬታውን ካስገባ የመፍትሔ ስብሰባ ቀጠሮ ማስያዝ አይጠበቅበትም።

**የፍትህ ሂደት ችሎቶች የሚካሄዱት ገለልተኛ በሆነ የችሎት ሹም ነው።**

የፍትህ ሂደት ቅሬታ ሊፈታ በማይችልበት ጊዜ፣ በገለልተኛ ሰሚ ሹም ወደሚመራ መደበኛ ችሎት ይመራል። የችሎቱ ሹሙ የፍትህ ሂደት ችሎቶችን እንዲያካሂድ በኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የሰለጠነ ጠበቃ መሆን አለበት።

የትምህርት ኤጀንሲው ለችሎት ሰሚ ሹሙ የሚሆነውን ወጪ ይከፍላል፤ ሆኖም ግን ይህ ግለሰብ ገለልተኛ፣ በዘፈቀደ የተመረጠ ሶስተኛ ወገን ነው። እሱ ወይም እሷ በትምህርት ውስጥ በሚሳተፍ የትምህርት ኤጀንሲ ተቀጥረው አይሰራም ወይም አትሰራም እና አንዱን ወገን ከሌላው የሚያስበልጥ የግልም ሆነ ሙያዊ ፍላጎት ላይኖረው ወይም ላይኖራት ይችላል።

በተጨማሪም፣ የችሎት ሰሚ ሹሙ IDEAን፣ የፌደራል እና የግዛት ህጎችን እና ደንቦችን እና ፍርድ ቤቶች የልዩ ትምህርት ጉዳዮችን እንዴት እንደሚተረጉሙ ጨምሮ የልዩ ትምህርት መስፈርቶችን በሚገባ ያውቃል።

ከችሎቱ በኋላ የችሎት ሰሚ ሹም በመደበኛ የሕግ አሠራር መሰረት ውሳኔ ይጽፋል።

### የመፍትሔ ስብሰባ

የመፍትሔ ስብሰባው አላማ በቅሬታው ላይ ስላሉት ችግሮች ለመወያየት እና የትምህርት ኤጀንሲው ከእርስዎ ጋር አብሮ መፍትሔ ለማምጣት ለመስራት እድል እንዲኖረው ለእርስዎ መልካም አጋጣሚን ለመስጠት ነው። የመፍትሔውን ስብሰባ ለመጥራት ኃላፊነቱ የትምህርት ኤጀንሲው ነው፣ እና እርስዎ መሳተፍ ይጠበቅብዎታል። እርስዎ በመፍትሔው ስብሰባ ላይ ካልተሳተፉ እና የትምህርት ኤጀንሲው የእርስዎን ተሳትፎ አለማድረግ ካስመዘገበ፣ የትምህርት ኤጀንሲው የ 30-ቀን ጊዜው ሲያልቅ የፍትህ ሂደት ቅሬታዎን ውድቅ እንዲያደርግ ችሎት ሰሚ ሹሙን ሊጠይቅ ይችላል።

እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የትኞቹ የIEP ቡድን አባላት በመፍትሔው ስብሰባ ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው ትወስናላችሁ። ይህ ስብሰባ ለትምህርት ኤጀንሲው ውሳኔዎችን የመስጠት ስልጣን ያለው የትምህርት ኤጀንሲ ተወካይን ማካተት አለበት።

የእርስዎን ጠበቃ ስብሰባው ላይ ለማግኘት ካልመረጡ በስተቀር የትምህርት ኤጀንሲው ጠበቃ በዚህ ስብሰባ ላይ አይሳተፍም። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የመፍትሔ ስብሰባውን ለመተው በጽሁፍ ካልተስማማችሁ፣ ወይም እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በመፍትሔ ስብሰባው ምትክ ሽምግልናን ለመጠቀም ካልተስማማችሁ በስተቀር ይህ ስብሰባ በመፍትሔ ሂደቱ ውስጥ የሚፈለግ እርምጃ ነው። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ሁለታችሁም ይህን ለማድረግ ከተስማማችሁ የ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜን ለማለፍ መስማማት ተፈቅዶላችኋል። ይህም የ 45-ቀን የፍትህ ሂደት ችሎት እና የውሳኔ የጊዜ ሰሌዳ እንዳይጀምር ይከላከላል።

እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው አለመግባባታችሁን በመፍትሔ ስብሰባው ላይ ከፈታችሁ፣ ሁለታችሁም በሕጋዊ መንገድ አስገዳጅ ስምምነትን መፈረም አለባችሁ፣ ይህም ስምምነት፡-

- አሁን ምን እንደከሰት በጽሑፍ ያስቀምጣል።
- በሁለቱም በእርስዎ እና በትምህርት ኤጀንሲ ተወካይ ይፈረማል።
- ፍርድ ቤት ሊያስፈፅም ይችላል

ሕጋዊ አስገዳጅ ማለት እርስዎ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው በስምምነቱ ካልተገዛችሁ፣ ፍርድ ቤት እርስዎም ሆኑ የትምህርት ኤጀንሲው በስምምነቱ እንድትገዙ ሊጠይቅ ይችላል።

እርስዎ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው ስምምነቱን ከፈረማችሁ በኋላ ላለመስማማት ከወሰናችሁ፣ አንዳችሁ ስምምነቱን በፈረማችሁ በሶስት የስራ ቀናት ውስጥ መሰረዝ ትችላላችሁ።

እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜው ከማብቃቱ በፊት በፍትህ ሂደት ቅሬታ ላይ ስምምነት ላይ ከደረሳችሁ፣ ቅሬታው ይዘጋል እና ምንም አይነት የፍትህ ሂደት አይካሄድም።

# የፍትህ ችሎት ሂደቱ

ለፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ቀጠሮ መ'ያዝ ይኖርበታል እና ችሎቱ ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው ምቹ በሆነ ቦታ እና ሰዓት መካሄድ አለበት። በችሎቱ ሂደት ውስጥ ግንኙነት በሚያስፈልግበት ጊዜ ገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ እርስዎን እና የትምህርት ኤጀንሲውን በተመሳሳይ ጊዜ ያነጋግራችኋል። በሌላ አነጋገር፣ በገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ፣ በእርስዎ እና በትምህርት ኤጀንሲው መካከል የሚደረጉት ሁሉም ግንኙነቶች በአንድ ላይ የሚፈጸሙ እንጂ ተነጣጥለው የሚደረጉ አይደሉም።

የ 45-ቀን የጊዜ ሰሌዳ የፍትህ ሂደት ችሎትን እና ገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚሆን የጊዜ መስኮትን ያካትታል። የ 45-ቀን የፍትህ ሂደት ችሎት የጊዜ ሰሌዳው የሚጀምረው የ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜ ካለቀ በኋላ፣ ወይም ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከተከሰተ በኋላ ነው፡-

- እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የመፍትሔውን ስብሰባ ለመተው (ላለማካሄድ) በጽሁፍ ከተስማማችሁ፣ ወይም
- አንዴ በችግሮቹ ላይ በመፍትሔ ስብሰባ ወይም በሽምግልና ስብሰባ ላይ መወያየት ከጀመራችሁ፣ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ምንም አይነት ስምምነት ሊኖር እንደማይችል በጽሁፍ ከተስማማችሁ፣ ወይም
- እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ከ 30-ቀን የመፍትሔ ጊዜው በላይ ለመሄድ በጽሁፍ ከተስማማችሁ በዚህም እርስዎ ሽምግልናን እንዲቀጥሉ፣ እና ወይ እርስዎ ወይ ደግሞ የትምህርት ኤጀንሲው ከሽምግልና ሂደቱ ከወጣችሁ።

ገለልተኛ የችሎት ሹሙ ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት ካልተስማማ (ወይም በሌላ አነጋገር ማራዘሚያ ካልሰጠ) በስተቀር፣ ከሁለቱ ወገኖች አንዱ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት በ 45 ቀናት የችሎት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ የሚከተለው ይከናወናል፡-

- ችሎቱ መካሄድ አለበት።
- የችሎት ውሳኔ ላይ መደረስ አለበት፤ እና
- የውሳኔው ቅጂ ለሁለታችሁም ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው፣ እንዲሁም ለኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) በተረጋገጠ ፖስታ መላክ አለበት።

የፍትህ ሂደቱ ከመድረሱ አምስት ቀናት በፊት፣ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው መረጃ ይፋ የሚሆንበት ኮንፈረንስ ላይ መሳተፍ አለባችሁ። ይህ ውይይት እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በችሎቱ ላይ የሚቀርበው መረጃ እንዳለዎት ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

## የፍትህ ሂደት ችሎት መብቶች

በፍትህ ሂደት ችሎት ላይ፣ የሚከተሉትን የማድረግ መብት አለዎት፡-

- የችሎቱ ጉዳይ የሆነው ልጅዎ እንዲገኝ ማድረግ
- ችሎቱ ለህዝብ ክፍት እንዲሆን መጠየቅ
- ጠበቃዎ ወይም የአካል ጉዳተኛ ልጆች ልዩ እውቀት ያላቸው ሰዎች ከእርስዎ ጋር እንዲሆኑ እና እንዲመክሩዎት ማድረግ

- ማስረጃ (ማረጋገጫ) ማቅረብ፣ ፊት ለፊት መጋፈጥ፣ እና ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ መጠየቅ (ጥያቄ) እና ምስክሮች እንዲገኙ መጠየቅ (በድጋሚ፣ ችሎቱ በፍትህ ሂደት ቅሬታዎ ላይ ያነሷቸውን ጉዳዮች ብቻ ይመለከታቸዋል፣ የትምህርት ኤጀንሲው አዳዲስ ጉዳዮችን እንዲያነሱ ካልፈቀደልዎት በስተቀር)
- ችሎቱ ከመድረሱ ከአምስት የስራ ቀናት በፊት እርስዎ እንዲያዩት ያልተደረገውን ማንኛውም ማስረጃ እንዳይቀርብ መከልከል
- እርስዎ ምንም ወጪ ሳይጠየቁ፣ ቃል-በቃል የተጻፈውን (ወይም ከመረጡ በኤሌክትሮኒክ ) የችሎቱን ቅጂ እና ማናቸውንም የግኝቶች እና የውሳኔ መዝገቦችን ይቀበላሉ።

**የሕግ ባለሙያ ባልሆኑ ማናቸውም ተሟጋቾች ታጅበው ከሆነ**

እርስዎ የሕግ ባለሙያ ባልሆኑ ማናቸውም ተሟጋቾች ታጅበው የሚሄዱ ከሆነ፣ እነዚህ ግለሰቦች ከሌላኛው ወገን የጠበቃ (የሕግ ባለሞያ) ክፍያዎችን (ወይም ለአገልግሎታቸው ማንኛውንም ክፍያ) የመቀበል መብት የላቸውም። ተሟጋቹ በችሎቱ ላይ ሕግን መተግበር አይችሉም እና በችሎት ሂደቱ ወቅት የተሟጋቹ ተሳትፎ ሊገደብ ይችላል።

# የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ቅሬታዎች እና የጊዜ ሰሌዳ

የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት የተወሰኑ የልዩ ትምህርት አለመግባባቶችን በተሳለጠ ሁኔታ ለመፍታት የሚያስችል ፈጣን የጊዜ ሰሌዳ ያለው ችሎት ነው። በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ እርስዎ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው የተፋጠነ የፍትህ ሂደት እንዲታይ ጥያቄ ማቅረብ የምትችሉት፡-

1. ስለ ልጅዎ የትምህርት ምደባ (ፕሮግራም ወይም አገልግሎቶች) የትምህርት ኤጀንሲ በሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ፣ እና ይህ ትምህርት ቤቱ በልጅዎ ላይ የወሰደው የዲሲፕሊን ቅጣት ውጤት ሲሆን፤ ወይም
2. እርስዎ በየባህርይ መገለጫን የመወሰን ስብሰባ ውጤቶች ካልተስማሙ፤ ወይም
3. የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎ የአሁኑ የትምህርት ምደባ (ፕሮግራም ወይም አገልግሎቶች) በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ በጣም እንደሚችል ሲያምን ብቻ ነው።

የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ቅሬታ የጊዜ ሰሌዳ የ 15 የቀን መቁጠሪያ ቀናት የመፍትሔ ጊዜ እና የ 20 የትምህርት ቀናት ችሎት የመስማት ጊዜን ያካትታል። የትምህርት ኤጀንሲው የፍትህ ሂደት ቅሬታ በደረሰው በሰባት የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ስብሰባ ለማድረግ መርሐግብር ማስያዝ አለበት። የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት ካለቀ በኋላ፣ ችሎት ሰሚ ሹሙ የመጨረሻ ውሳኔውን ለመፃፍ እና ለእርስዎ እና ለትምህርት ኤጀንሲው ለመስጠት 10 የትምህርት ቀናት አሉት። በተፋጠነ የፍትህ ሂደት ቅሬታ ወቅት ምንም ተጨማሪ ጊዜ አይጨመርም።

# ውሳኔን ይግባኝ ማለት

ውሳኔው በተደረሰ በ 45 ቀናት ውስጥ የተጎዳው ወገን በቀጥታ በኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር፣ የፍትህ ሂደት ችሎት ሲጠናቀቅ በገለልተኛ ሰሚ ሹሙ የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው። የተጎዳው ወገን ወላጅ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው ነው ይህም የሰሚ ሹሙ ውሳኔ ለዚያ ወገን የማይመች ይሆናል (ማለትም ያ ወገን አላሸነፈም ማለት ነው)።

## የችሎት ሰሚ ሹሙን ውሳኔዎች እንዴት ይግባኝ ማለት እንደሚቻል

የችሎት ሰሚ ሹሙን ውሳኔ ይግባኝ ለማለት፣ የይግባኝዎን ግልባጭ በጽሑፍ ለመምሪያው እና የይግባኙን ቅጂ ለትምህርት ኤጀንሲዎ የበላይ ተቆጣጣሪ (superintendent) መላክ ወይም ኢሜይል ማድረግ አለበት። መምሪያው የፍትህ ሂደት ውሳኔን በገለልተኝነት ለመመርመር የግዛት ደረጃ የግምገማ ሹም (ወይም “የግምገማ ኦፊሰር”) ይሰይማል። የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ለግምገማ ሹሙ ይከፍላል።

የግምገማ ሹሙ የፍትህ ሂደት ችሎቱን መዝገቦች ይመረምራል። በተጨማሪም፣ የግምገማ ሹሙ ችሎቱ የፍትህ ሂደት መስፈርቶችን መከተሉን ያረጋግጣል እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ማስረጃ ይፈልጋል። የግምገማ ሹሙ ከእርስዎ እና ከትምህርት ኤጀንሲው የቃል ወይም የጽሁፍ ክርክሮችን ሊጠይቅ ይችላል። የግምገማ ሹሙ የቃል ክርክርን ለመመልከት ችሎት ካካሄደ፣ በፍትህ ችሎት ሂደት የሚሰጡዎት ሁሉም የችሎት ሰሚ መብቶች (ገጽ 25 ይመልከቱ) በተመሳሳይ መልኩ በግምገማ ሹም ችሎት ሰሚ ፊት የሚሰጡዎት የችሎት መብቶች ናቸው።

### የጊዜ ሰሌዳ/ማራዘሚያዎች

መምሪያው የእርስዎ የግዛት ደረጃ ግምገማ ጥያቄ በደረሰው በ 30 ቀናት ውስጥ የግምገማ ሹሙ ውሳኔ ይሰጣል፣ እሱ ወይም እሷ ማራዘሚያ ካልሰጡ በስተቀር፣ ይህም በወላጅ ወይም በትምህርት ኤጀንሲው ሊጠየቅ ይችላል (ነገር ግን፣ ከተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት ይግባኝ በሚቀርብበት ጊዜ የጊዜ ማራዘሚያዎች ሊደረጉ እንደማይችል ልብ ይበሉ)። እንዲሁም እርስዎ የሁለቱንም የግምገማ ሹሙ ግኝቶችን እና ውሳኔዎችን የጽሁፍ ቅጂዎች ወይም የቃል-በቃል ኤሌክትሮኒክ ቅጂ መዝገቦችን መጠየቅ ይችላሉ።

### ለፌዴራል ወይም ለግዛት ፍርድ ቤት ይግባኝ

ለፌዴራል ወይም ለግዛት ፍርድ ቤት ይግባኝ ካልቀረበ በስተቀር በግዛት ደረጃ የሚሰጠው የግምገማ ውሳኔ የመጨረሻ ነው። በግምገማ ሹም ውሳኔ የተጎዳው አካል (ያላሸነፈው) የግምገማ ሹሙ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ 90 ቀናት ውስጥ በፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ወይም የግምገማ ሹሙ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ 45 ቀናት ውስጥ የልጅዎ የትምህርት ኤጀንሲ በሚገኝበት የካውንቲው የጋራ አቤቱታ ማቅረቢያ ፍርድ ቤት ክስ የመመስረት መብት አለው። ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይመረምራል፣ በተከራካሪ ወገኖች ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰማል፣ እና መዝገቦቹንና የቀረበውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል። በፍርድ ቤት ላቀረቡት ይግባኝ የፍርድ ቤት ወጪዎችን እርስዎ መክፈል አለቦት፣ ነገርግን እርስዎ ካሸነፉ የፍርድ ቤት ክፍያዎችን እና የጠበቃ ክፍያዎችን በፍርድ ቤቱ ውሳኔ አማካኝነት ሊያገኙ ይችላሉ።

## በፍትህ ሂደት ችሎት ወቅት የልጅ ሁኔታ

- እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎ የትምህርት ምደባ ሊቀየር እንደሚችል ካልተስማማችሁ በስተቀር የፍትህ ሂደት ቅሬታ በሂደት ላይ እያለ ልጅዎ አሁን ባለው የትምህርት ምደባ ውስጥ መቆየት ወይም ባለበት ሆኖ መቀጠል አለበት።
- የልጅዎ የአሁኑ የትምህርት ምደባ በቅርብ ጊዜ በተተገበረው የእሱ ወይም የእሷ IEP ውስጥ የተገለጸው ነው።
- በትምህርት ኤጀንሲው የዲሲፕሊን ቅጣት ምክንያት ልጅዎ በ IAES (ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ፣ ወይም ከትምህርት ቤቱ ውጭ ጊዜያዊ የመማሪያ ሁኔታ) ውስጥ ከተመደበ፣ የችሎቱ ሹሙ ውሳኔ እስኪሰጥ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎ የዲሲፕሊን ቅጣቱ እስኪያበቃ ድረስ፣ ልጅዎ በዚያ የትምህርት ሁኔታ ውስጥ ይቆያል።
- የፍትህ ሂደት ቅሬታው መጀመሪያ ወደ ትምህርት ኤጀንሲ መግባትን የሚያካትት ከሆነ፣ ልጅዎ ከእርስዎ ፈቃድ ጋር፣ የፍትህ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በትምህርት ኤጀንሲው ውስጥ መቀመጥ አለበት።
- ልጅዎ ሶስት አመት ስለሞላው እና በህጉ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ክፍል ስር አገልግሎቶችን ከዚህ በኋላ ለማግኘት ብቁ ስላልሆነ የፍትህ ሂደት ቅሬታው በህጉ የትምህርት እድሜ ስር አገልግሎቶችን ለመጀመር ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎ ያላገኛቸውን የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን የመስጠት ግዴታ የለበትም።
- ልጅዎ ለልዩ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ወላጁ ለመጀመሪያው አገልግሎት መሰጠት ፈቃደኛ ከሆነ፣ የትምህርት ኤጀንሲው በወላጅ እና በትምህርት ኤጀንሲው መካከል አለመግባባት የሌለባቸውን አገልግሎቶች መስጠት አለበት።
- የግምገማ ሹሙ የምደባ ለውጥ ተገቢ እንደሆነ ከእርስዎ ጋር ከተስማማ፣ ምደባው በግዛቱ እና በወላጆች መካከል ባለበት እንዲቀጥል በሚል ዓላማ እንደተደረገ ስምምነት ተደርጎ መወሰድ አለበት።

**የገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹም ውሳኔን ይግባኝ ለመጠየቅ**

እርስዎ የገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ (ይግባኝ) ውሳኔው በደረሰዎ በ 45 የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ መቃወም ይችላሉ። ይግባኝዎን ወደዚህ ይላኩ፦-

የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ የልዩ ልጆች ቢሮ የክርክር መፍታት ክፍል (Ohio Department of Education and Workforce
Office for Exceptional Children Dispute Resolution Section)
25 South Front Street Mail Stop 409
Columbus, Ohio 43215
OECdueprocess@education.ohio.gov

ለተጨማሪ እርዳታ፣ እባክዎን ወደ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) የልዩ ልጆች ቢሮ በ (614) 466-2650 ይደውሉ፣ ወይም ከክፍያ ነጻ በ (877) 644-6338 ይደውሉ።

# የአቃቤ ህግ ክፍያዎች

በማንኛውም ጊዜ በፍትህ ሂደት (ወይም በፍትህ ሂደት ውሳኔ ይግባኝ በሚሉ የችሎት ሂደቶች) እርስዎን የሚወክል ጠበቃ (የሕግ ባለሙያ) ለመቅጠር መምረጥ ይችላሉ፣ ነገርግን የራስዎን ህግ ነክ ወጪዎች መክፈል አለብዎት። እርስዎ ጠበቃ ለመቅጠር ከመረጡ እና ከፍትህ ሂደት ጋር በተገናኘ በፌዴራል ወይም በግዛት ፍርድ ቤት እርምጃ ወይም የችሎት ሂደት እርስዎ አሸናፊ (አመቺ ውሳኔ ከተቀበሉ) ከሆኑ (እርስዎን የበላይ ወገን ካደረግዎት)፣ ፍርድ ቤቱ የትምህርት ኤጀንሲውን ምክንያታዊ የጠበቃ ክፍያዎችን ለእርስዎ እንዲከፍል ሊያዝዘው ይችላል።

## የትምህርት ኤጀንሲው ካሸነፈ

የትምህርት ኤጀንሲው ካሸነፈ፣ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ የሆኑትን የጠበቃ ክፍያዎች ለትምህርት ኤጀንሲው እርስዎ እንዲከፍሉ ሊያዝዎት ይችላል። ፍርድ ቤቱ እርስዎ ወይም ጠበቃዎ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ወይም የትምህርት ኤጀንሲዎ የጠበቃ ክፍያዎችን እንድትከፍሉ ሊያዝዝ ይችላል እና ይህም የሚሆነው እነሱ ካሸንፉ እና ፍርድ ቤቱ ከሚከተሉት አንዱን ከወሰነ ነው፡-

- እርምጃው ተራ፣ ምክንያታዊነት የጎደለው፣ ወይም መሰረት የሌለው ከነበረ
- እርምጃው በግልጽ ተራ፣ ምክንያታዊነት የጎደለው፣ ወይም መሰረት የሌለው ከሆነ በኋላ እርስዎ ህጋዊ እርምጃ ማምጣትዎን ከቀጠሉ
- እርምጃው ላልተገባ ዓላማ ማለትም እንደ ትንኮሳ፣ አላስፈላጊ መዘግየት፣ ወይም ያለፍላጎት የህግ ወጪዎችን መጨመር የቀረበ ከነበረ

**ፍርድ ቤቱ ህጋዊ ክፍያዎች ለእርስዎ ወይም ለትምህርት ኤጀንሲው እንዲከፈሉ ካዘዘ**

ፍርድ ቤቱ ህጋዊ ክፍያዎች ለእርስዎ ወይም ለትምህርት ኤጀንሲው ተመልሰው እንዲከፈሉ ካዘዘ፣ ፍርድ ቤቱ ምክንያታዊ የሆነውን መጠን ይወስናል። የጠበቃ ክፍያዎች የፍርድ ክሱ ወይም የችሎት ሂደቱ በቀረበበት ማህበረሰብ ውስጥ ባሉ የተለመዱ ተመኖች እና በተሰጠው የአገልግሎት አይነት እና ጥራት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት። በፍርድ ቤቱ የጠበቃ ክፍያዎችን የመስጠት ችሎታ ላይ የተወሰኑ ገደቦች አሉ።

ፍርድ ቤት በነዚህ ሁኔታዎች ላይ የጠበቃ ክፍያዎችን መስጠት አይችልም፡-

- የትምህርት ኤጀንሲው ክርክሩን የችሎት ሂደቱ በቀጠለ በ 10 ቀናት ውስጥ ለመፍታት ፍላጎቱን በጽሁፍ ሲያቀርብ፣ እርስዎ በ 10 ቀናት ውስጥ ይህንን የቀረበሎትን ካልተቀበሉ፣ እና በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የትምህርት ኤጀንሲው ካቀረበው እልባት ይልቅ ለእርስዎ ያነሰ ጠቃሚ በሚሆንበት ሁኔታ።
    - ይሁን እንጂ፣ እርስዎ በእርምጃው ዳኝነት ካሸነፉ እና ፍርድ ቤቱ የትምህርት ኤጀንሲውን የክርከር ማሳረጊያ አቅርቦት ላለመቀበል (በቂ ምክንያት ካልዎት) ከወሰነ፣ ፍርድ ቤት ክፍያዎችን ለእርስዎ ሊያጎናጽፍ ይችላል።
- ለጠበቃዎ በ IEP ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ፣ ያ ስብሰባ በአስተዳደራዊ ችሎት ወይም በፍርድ ቤት እርምጃ ካልተጠራ በስተቀር
- በመፍትሔ ስብሰባ ላይ ለጠበቃዎ ተሳትፎ

**የጠበቃ ክፍያዎችን መቀነስ**

ፍርድ ቤቱ የሚከተለው ከሆነ የጠበቃ ክፍያዎችን ሊቀንስ ይችላል፡-

- በችሎት ሂደቱ እርስዎ ወይም ጠበቃዎ ለክርክሩ የመጨረሻውን መፍትሔ ያለምክንያት ካዘገያችሁት
- ተመጣጣኝ ክህሎት፣ ዝና፣ እና ልምድ ባላቸው ጠበቆች ለተመሳሳይ አገልግሎቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ዋጋ በሰዓት ከሚከፈለው ዋጋ ምክንያታዊ ባልሆነ መልኩ የጠበቃዎ ክፍያ መጠን ከፍ ያለ ከሆነ
- የእርምጃውን ወይም የችሎት ሂደቱን ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት የወሰዳችሁት ጊዜ እና ህጋዊ አገልግሎቶች ከልክ ያለፉ (በጣም ብዙ) ከነበሩ
- ጠበቃዎ በቅሬታ ማስታወቂያዎ ላይ ተገቢውን መረጃ ለትምህርት ኤጀንሲው ካልሰጡ

ፍርድ ቤቱ ግዛቱ ወይም የትምህርት ኤጀንሲው ያለምክንያት የእርምጃውን ዳኝነት ወይም የችሎት ሂደቱን የመጨረሻ ውሳኔ እንዳዘገዩ ወይም በሌላ መልኩ የIDEAን የሥርዓት ጥበቃዎች መጣሳቸውን ካገኘ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ውስጥ የትኛውም ተፈጻሚ አይሆንም።

# ዲሲፕሊን

## የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ልጆች የሚሆኑ የዲሲፕሊን ሂደቶች

በአንዳንድ ሁኔታዎች የትምህርት ኤጀንሲዎ የአካል ጉዳት ላለበት ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠቱን መቀጠል ሊኖርበት ይችላል፣ ሌላው ቀርቶ የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን አሁን ካለበት የትምህርት ምደባው ካቋረጠው፣ ካባረረው፣ ወይም በሌላ መንገድ ካስወገደው በኋላም ቢሆንም እንኳን (አሁን ስላለው ስለልጅዎ የትምህርት ምደባ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የልጅዎን IEP ይመልከቱ)።

### የትምህርት ምደባ እና አማራዎች

ልጅዎ ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት ላነሰ ጊዜ ውስጥ የትምህርት ኤጀንሲ ደንቦችን በመጣስ አሁን ካለበት ወይም ካለችበት የትምህርት ምደባ ከወጣ/ች፣ የትምህርት ኤጀንሲው በዚያ ጊዜ ውስጥ ለልጅዎ ልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠት አይጠበቅበትም። ልጅዎ *ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ* ከትምህርት ቤት ከተባረረ፣ በሌላ የትምህርት ቦታ (ለምሳሌ፣ ሌላ ክፍል፣ ህንፃ ወይም የተማሪው ቤት) ቢሆንም እንኳን፣ ትምህርት ቤቱ ለልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መስጠቱን መቀጠል ይኖርበታል።

የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን ከ 10 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ አሁን ካለበት/ካለችበት ምደባ ካስወገደ፣ እንደ የልጅዎ የትምህርት ምደባ ለውጥ ተደርጎ ይቆጠራል።

የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን አሁን ካለበት የትምህርት ምደባ በተለዩ አጋጣሚዎች (ተከታታይ መወገዶች) ካስወገደ፣ ይህም ድምሩ በአንድ የትምህርት አመት ውስጥ ከ 10 ቀናት በላይ ሲሆን፣ እነዚያ ማባረሮች የልጅዎን የትምህርት ምደባ ለውጥ የሚያስመጡ ከሆነ ትምህርት ቤቱ መወሰን አለበት።

ትምህርት ቤቱ ይህን ውሳኔ ሲያደርግ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡-

- ልጅዎ በተወገደ ቁጥር ያለው ርዝማኔ
- ልጅዎ የተወገደበት ጠቅላላ ጊዜ
- መወገዶቹ ምን ያህል የተቀራረቡ እንደነበር
- የልጅዎ ባህሪ እና ከእሱ ወይም ከእሷ በተወገደባቸው ቀደም ካሉት አጋጣሚዎች ባህሪ ጋር ያለው ተመሳሳይነት

ልጅዎ የትምህርት ቤት ህጎችን ስላልተከተለ የልጅን የትምህርት ምደባ ሲቀይሩ የትምህርት ኤጀንሲው፣ ወላጅ እና የሚመለከታቸው የIEP ቡድን አባላት፣ በወላጅ እና በትምህርት ኤጀንሲው እንደተወሰነው የባህርይ መገለጫን የመወሰን ስብሰባ ለማካሄድ መገናኘት አለባቸው። የባህርይ መገለጫን የመወሰን ስብሰባ ዓላማ የልጅዎ ባህሪ የተከሰተው በአካል ጉዳተኝነቱ መሆኑን ወይም ባህሪው ከልጅዎ አካል ጉዳተኝነት ጋር ቀጥተኛ እና ተጨባጭ ግንኙነት ያለው መሆኑን ለመወሰን ነው።



# የባህርይ መገለጫን የመወሰን ስብሰባ

በዲሲፕሊን ምክንያቶች የልጅዎን የትምህርት ምደባ ከመቀየርዎ በፊት፣ የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን መብቶች ለመጠበቅ የተወሰኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። አንዱ እርምጃ የባህርይ መገለጫን የመወሰን ስብሰባ ማካሄድ ነው። ይህ ስብሰባ የልጅዎ ባህሪ የተከሰተው በአካል ጉዳቱ ነው ወይም ባህሪው ከልጅዎ አካል ጉዳተኝነት ጋር ቀጥተኛ እና ተጨባጭ ግንኙነት ያለው መሆኑን ለመወሰን የሚደረግ ስብሰባ ነው። በሌላ አነጋገር፣ የልጅዎ ባህሪ በእሱ ወይም በእሷ አካል ጉዳተኝነት የተከሰተ ነውን? የተማሪው IEP ቡድን የልጅዎ ባህሪ በአካል ጉዳተኝነት የተከሰተ እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ የትምህርት ምደባውን ለመቀየር በሚደረግ ማናቸውም ውሳኔ ባሉት በ 10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ይወስናል።

## የባህርይ መገለጫን የመወሰን ግምገማ ስብሰባ

የባህርይ መገለጫን የመወሰን ግምገማ ስብሰባ ላይ፣ እርስዎ እና ሌሎች የIEP ቡድን አባላት የልጅዎን IEP፣ የአስተማሪ ምልከታዎችን እና በእርስዎ የቀረበውን ማንኛውንም ተዛማጅ መረጃ ጨምሮ አስፈላጊውን መረጃ ይገመግማሉ።

ባህሪው የልጅዎ የአካል ጉዳት መገለጫ ከሆነ፣ የIEP ቡድኑ የምደባ ለውጥ ለማድረግ ካልተስማማ በስተቀር ልጅዎ ወደ ተወገደበት ቦታ ይመለሳል።

የልጅዎ ባህሪ የአካል ጉዳቱ መገለጫ ሆኖ ከተገኘ፣ የ IEP ቡድን የሚከተለውን ማድረግ አለበት፦

1. የተግባራዊ ባህሪ ግምገማ በ 10 ቀናት ውስጥ መጀመር እና በተቻለ ፍጥነት ማጠናቀቅ አለበት። ተግባራዊ የባህሪ ምዘና የልጅዎን ባህሪ መገምገም ሲሆን በልጅዎ አካባቢ ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ባህሪን የሚቀሰቅሰው ምን እንደሆነ እና እንዲሁም ልጅዎ አወንታዊ ውጤቶችን እና ግብረመልሶችን እንዲያገኝ የትኞቹን የመተካት ባህሪዎች ማስተማር እንደሚይስፈልግ ለመወሰን ይጠቅማል።
2. የተግባራዊ ባህሪ ምዘናው ቀድሞውኑ ከተጠናቀቀ እና ከተያዘው ዲሲፕሊን ጋር የተያያዘ ከሆነ (የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ለትምህርት ቤት ተገቢ ያልሆኑ ባህሪያትን እና ትምህርት ቤቱ እነሱን ለመቀነስ የሚሞክራቸውን ልዩ መንገዶች የሚመለከት ከሆነ) ለልጅዎ የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ይጀምሩ፣ ወይም

3. የባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ አስቀድሞ ካለ፣ እቅዱን ይከልሱ እና በ 10 ቀናት ውስጥ አስፈላጊ ለውጦችን ያድርጉ።

## ጊዜያዊ አማራጭ (ጊዜያዊ እና ልዩ ልዩ) የትምህርት ሁኔታ

ልጅዎን በጊዜያዊ ተለዋጭ የትምህርት ሁኔታ (IAES) የማስቀመጥ ውሳኔ የሚወሰነው በልጅዎ IEP ቡድን ነው። IAES ልጅዎ ልዩ ትምህርትን የሚቀበልበት የተለየ እና ጊዜያዊ ምደባ ነው። ልጅዎ የትምህርት ቤት ህግን ስለጣሰ የIEP ቡድኑ የልጅዎን ምደባ ወደ IAES ለመቀየር ውሳኔ ባደረገበት ቀን የትምህርት ኤጀንሲው ስለ ውሳኔው ማሳወቅ እና በልዩ ትምህርት የወላጅ መብቶች መመሪያውን ሊሰጥዎ ይገባል።

የልጅዎ ባህሪ በልጅዎ የአካል ጉዳት ምክንያት የተከሰተ ቢሆንም እንኳን፣ ልጅዎ የሚከተሉትን አድርጎ ከትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን ወደ IAES እስከ 45 የትምህርት ቀናት ሊያግደው ይችላል።

- የጦር መሣሪያ ይዞ ከተገኘ
- እያወቀ ህገወጥ እጾችን ይዞ ከሆነ ወይም ከተጠቀመ፣ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበትን ንጥረ ነገር (ለምሳሌ ናርኮቲክስ) ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ከሞከረ
- በሌላ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ካደረሰ

ይህ በአጠቃላይ ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት በሚወስደው መንገድ፣ በትምህርት ቤት፣ ወይም በትምህርት ቤት ተግባር ላይ ድርጊቱን ፈፅሞ መሆን አለመሆኑን ይመለከታል።

የልጅዎ ባህሪ *በልጅዎ አካል ጉዳተኝነት በቀጥታ የተከሰተ ካልሆነ*፣ አንድ የአካል ጉዳተኝነት የሌለው ልጅ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚቀበልበትን ጊዜ ያህል ልጅዎ በ IAES ውስጥ ሊቀመጥ ይችላል።

### የልጅዎ ባህሪ በተጠረጠረ የአካል ጉዳት ምክንያት በሚሆንበት ጊዜ

ልጅዎ IEP ከሌለው፣ ልጅዎ የትምህርት ቤት ህግን ከመጣሱ በፊት ከሚከተሉት ነገሮች መካከል አንዱ የተከሰተ ከሆነ ልጅዎን እንደ አካል ጉዳተኛ ልጅ እንዲይዝ ትምህርት ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ፦

- ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎት ሊፈልግ ይችላል ብለው እንደሚያስቡ፣ ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች ወይም ለልጅዎ መምህር በጽሁፍ ነግረውት ከነበረ፣ ወይም
- እርስዎ ለልጅዎ ግምገማ እንዲደረግለት ጠይቀው ከነበረ፤ ወይም
- የልጅዎ መምህር ወይም ሌላ የት/ቤት ሰራተኛ ስለልጅዎ የስነምግባር ሁኔታ ልዩ ስጋቶች ለልዩ ትምህርት ዳይሬክተሩ ወይም ለሌሎች ተቆጣጣሪ ሰራተኞች በቀጥታ ነግረው ከነበረ።
- የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን ለልዩ ትምህርት እንዲገመግም ፈቃድ ለመስጠት እርስዎ ፈቃደኛ ካልሆኑ ኤጀንሲው ልጅዎን እንደ አካል ጉዳተኛ ልጅ እንዲይዝ አይጠበቅም። እንዲሁም እርስዎ ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ለመቀበል ፈቃደኛ ካልነበሩ ወይም ልጅዎ ከተገመገመ እና ቡድኑ ልጅዎ የአካል ጉዳት እንደሌለበት ወስኖ ከነበረ ይህ የተባለው ሁኔታ እውነት ነው። የትምህርት ኤጀንሲው ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸውን አካል ጉዳተኝነት የሌለባቸውን ተማሪዎች በሚቀጣበት መልኩ ልጅዎን በዲሲፕሊን ሊቀጣ ይችላል።

የልጅዎ ባህሪ *ከልጅዎ አካል ጉዳተኝነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ወይም የተከሰተ ከሆነ* እና ልጅዎ የትምህርት ቤት ህጎችን ከጣሰ፣ እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው በባህሪ ጣልቃገብነት እቅድ ወይም IEP አካል መሰረት ለምደባ ለውጥ ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ ልጅዎ ወደ ተወገደበት የትምህርት ሁኔታ መመለስ አለበት።

ነገር ግን፣ የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን አሁን ባለው የትምህርት ምደባ (በልጅዎ IEP መሰረት) ማቆየት በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል ብሎ ካመነ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ስለዚህ ጉዳይ ለመወያየት የIEP ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። እርስዎ እና የትምህርት ኤጀንሲው ስለ ምደባ ለውጥ ካልተስማማችሁ፣ የትምህርት ኤጀንሲው የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት እንዲካሄድ ሊጠይቅ ይችላል — በሌላ አነጋገር በቶሎ መፍትሄ ለማግኘት በፍጥነት የሚካሄድ የፍትህ ሂደት ችሎት ሊጠይቅ ይችላል (የተፋጠነ የፍትህ ሂደትን በገጽ 25 ላይ ይመልከቱ)።

## እርስዎ የትምህርት ቦታ ምደባ ለውጥ ወይም ከባህርይ መገለጫን የመወሰን ግምገማ ግኝት ጋር የማይስማሙ ከሆነ

በዲሲፕሊን ምክንያት የልጅዎን ወቅታዊ የትምህርት ሁኔታ ለመቀየር የተደረገን ውሳኔ ለመቃወም ወይም የባህሪ መገለጫን የመወሰን ግምገማን ለመቃወም የተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት መጠየቅ ይችላሉ (የፍትህ ሂደት  መረጃን በገጽ 25 ይመልከቱ)። የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን ምደባ ሲቀይር መስፈርቶችን የተከተለ መሆኑን ወይም የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎ ባህሪ የልጅዎ የአካል ጉዳት መገለጫ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ካሳየ ገለልተኛ የችሎት ሰሚ ሹሙ በተፋጠነ የፍትህ ሂደት ችሎት ጊዜ ይወስናል።

ከላይ እንደተገለፀው፣ የትምህርት ኤጀንሲው የልጅዎን ምደባ መቀጠል በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ካመነ የትምህርት ኤጀንሲው የተፋጠነ የፍትህ ሂደት እንዲካሄድ ሊጠይቅ ይችላል (የተፋጠነ የፍትህ ሂደት በገጽ 25 ይመልከቱ)።

# በሕዝብ ወጪ በግል ትምህርት ቤት በወላጆች የአካል ጉዳተኛ ልጆችን በአንድ ወገን መመደብ

## የገንዘብ ማካካሻን የመወሰን ሂደት

ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ለማስገባት ከመረጡ፣ የትምህርት ኤጀንሲው ለልጅዎ በትምህርት ኤጀንሲ ውስጥ ነፃ ተገቢ የሆነ የሕዝብ ትምህርት (FAPE) እስካቀረበ ድረስ፣ የትምህርት ኤጀንሲዎ በግል ትምህርት ቤት ለሚሰጡ የልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ክፍያን መክፈል የለበትም። የትምህርት ኤጀንሲው ለልጅዎ FAPE አልሰጠም ብለው ካመኑ፣ ችሎት እንዲካሄድ የሚሆንበት እና ገለልተኛ ችሎት ሰሚ ሹሙ የትምህርት ኤጀንሲው ለልጅዎ FAPE መስጠቱን ወይም አለመስጠቱን ውሳኔ የሚሰጥበት የፍትህ ሂደት ቅሬታ የማቅረብ አማራጭ አለዎት (የፍትህ ሂደት መረጃን በገጽ 24 ይመልከቱ)። የትምህርት ኤጀንሲዎ FAPEን ያላቀረበ መሆኑ በችሎቱ ጊዜ በገለልተኛ ሰሚ ሹሙ ከተወሰነ፣ ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ እርስዎ ያወጡት ወጪ እንዲካካስሎት (እንዲከፍሉዎት) መብት እንዳለዎት ችሎት ሰሚ ሹሙ ሊወስን ይችላል።

### የገንዘብ ማካካሻ ቅነሳ ወይም ማጣት

የትምህርት ኤጀንሲው ምን ያህል ገንዘብ እንዲከፍል ሊጠየቅ እንደሚችል ሊቀነስ ይችላል፣ ወይም ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ከተከሰተ እርስዎ የማካካሻ ክፍያውን ሙሉ በሙሉ ሊያጡ ይችላሉ፡-

- ልጅዎን ከትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት በተካሄደው የIEP ስብሰባ፣ በIEP ቡድኑ የቀረበውን የትምህርት ምደባ እንደማይቀበሉት እና ስለሚያሳስብዎ ነገሮች ካልነገሯቸው እና ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ እንዳቀዱ ለትምህርት ቤቱ ካልነገሩ።
- ልጅዎን ከትምህርት ኤጀንሲው ከማስወጣትዎ ቢያንስ ከ 10 የስራ ቀናት በፊት ለት/ቤቱ IEPን እየተቀበሉ እንዳልነበሩ እና ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ እንዳቀዱ  በጽሁፍ ካልነገሩ (እነዚህ 10 የስራ ቀናት በሳምንቱ ቀናት የሚከበሩ በዓላትን ያካትታሉ)
- ልጅዎን ከትምህርት ቤት ከማስወጣትዎ በፊት የትምህርት ኤጀንሲው ልጅዎን ለመገምገም ማቀዱን አግብብነት ያለው የጽሁፍ ማስታወቂያ ከሰጠዎት፣ እና ልጅዎን ለግምገማው እንዲገኝ ካላደረጉት
- ፍርድ ቤቱ እርስዎ ምክንያታዊነት የጎደለው ድርጊት እንደፈጸሙ ይወስናል

### የማካካሻ ገንዘብን ማስጠበቅ

ከሚከተሉት ውስጥ አንዳቸውም ቢከሰቱ የሚካካሰው ገንዘብ (ተመልሶ የሚከፈልዎት መጠን) ሊቀነስ አይችልም ወይም እርስዎ ክፍያውን ሊከለከሉ አይችልም፡-

- የትምህርት ኤጀንሲው እርስዎ ማስታወቂያ እንዳይሰጡ ከከለከልዎት
- የትምህርት ኤጀንሲው ማስታወቂያ መስጠት እንደሚጠበቅብዎት ነግሮዎት ካልነበረ
- ማስታወቂያውን መስጠት በልጅዎ ላይ አካላዊ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ።

እንዲሁም፣ ፍርድ ቤት ወይም ችሎት ሰሚ ሹሙ የሚከተሉት ነገሮች ከሆኑ እርስዎ ይህንን ማስታወቂያ ባለመስጠትዎ የማካካሻ ገንዘቡ እንደማይቀንስብዎት ወይም እንደማይከለከሉ ሊያውቁ ይችላሉ፡-

- እርስዎ በእንግሊዘኛ ማንበብም ሆነ መጻፍ ካልቻሉ፣ ወይም
- ማስታወቂያውን መስጠት በልጅዎ ላይ ከባድ የስሜት ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ።

# የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተማሪዎች ስለ ስኮላርሺፕ ፕሮግራሞች ለወላጆች ማሳወቂያ

## ማሳወቂያው ሲከሰት

የትምህርት ኤጀንሲው ለአካል ጉዳተኛ ልጅ ግምገማን ባጠናቀቀ ወይም የልጁን IEP ማዘጋጀት፣ መገምገም፣ ወይም ማሻሻል በጀመረ ቁጥር፣ የትምህርት ኤጀንሲው ስለ ኦቲዝም ስኮላርሺፕ ፕሮግራም (the Autism Scholarship Program) እና ስለ ጆን ፒተርሰን ስኮላርሺፕ ፕሮግራም (the Jon Peterson Scholarship Program) ሊነግሮት ይገባል።

### የኦቲዝም ስኮላርሺፕ ፕሮግራም (AUTISM SCHOLARSHIP PROGRAM)

ስለ ኦቲዝም ስኮላርሺፕ ፕሮግራም መረጃ ለማግኘት education.ohio.gov የሚገኘውን የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ድረ-ገጽን ይጎብኙ እና በፍለጋ ሳጥኑ ውስጥ ***AAutism Scholarship Program*** ብለው ይጻፉ ወይም ወደ autismscholarship@education.ohio.govኢሜይል ይላኩ።

### ጆን ፒተርሰን የልዩ ፍላጎቶች ስኮላርሺፕ ፕሮግራም (JON PETERSON SPECIAL NEEDS SCHOLARSHIP PROGRAM)

ልጅዎ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እየተቀበለ ከሆነ፣ እርስዎ ለጆን ፒተርሰን የልዩ ፍላጎት ፕሮግራም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ስለ ጆን ፒተርሰን የልዩ ፍላጎቶች ስኮላርሺፕ ፕሮግራም መረጃ ለማግኘት education.ohio.gov የሚገኘውን የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ድረ-ገጽን ይጎብኙ እና ***Jon Peterson Scholarship*** ብለው በፍለጋ ሣጥኑ ውስጥ ይጻፉ ወይም ወደ peterson.scholarship@education.ohio.gov ኢሜይል ይላኩ።

**ተጨማሪ መረጃ**

ስለ ስኮላርሺፕ ፕሮግራሞች መረጃ የኦሃዮ የትምህርት እና የሰራተኛ ኃይል መምሪያ (Ohio Department of Education and Workforce) ድረ-ገጽ education.ohio.gov ላይ ይገኛል።

በነዚህ የነፃ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ለጥያቄዎች የሕዝብ ያልሆኑ የትምህርት አማራጮች ቢሮን (The Office of Nonpublic Educational Options) በ (614) 466-5743 ወይም ከክፍያ ነፃ በ (877) 644-6338 ያነጋግሩ።